ማውጫ

ገጽ

መግቢያ 3
ክፍል አንድ 4

ክፍል ሁለት 7
2.1. የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ የሚባሉት ምንድን ናቸው? 8
2.2. በሃይማኖት መቆም ምን ማለት ነው? 8
2.3. መንፈሳዊ ልምምድ ምን ምንድን ናቸው? 9

ክፍል ሥስት 10
3.1 በክርስትና ዕለት ዕለት እንዴት መኖር እንችላለን? 10
3.2 በክርስትና ዕለት ዕለት ለመኖር ምን ከማድረግ እንጀምር? 10
3.3 የጸሎት ቤት እንዴት እናዘጋጅ? 11

ክፍል አራት 14
4.1 የጸሎት መርሃ ግብርና ሰዓታት 14

ክፍል አምስት 19
5.1 የጸሎት ክፍልና ቤተመቅደስ ምን ያገናኛቸዋል? 19

ክፍል ስድስት 21
6.1 ስግደት 21
6.2 ስግደት ስንት አይነት ነው? 22
6.3 ስግደት በስንት ይከፈላል? 23

ክፍል ሰባት 24
ስግደት 24
7.1 የአምላክ ስግደት 24
7.2 የአምልኮ ስግደት መቼ መቼ ይሰገዳል? 25
7.3 የአምልኮ ስግደት እንዴት ይሰገዳል? 25
7.4 የአምልኮ ስግደት ምን ምን እያልን እንሰገድ? 26

ክፍል ስምንት 30
8.1 የንስሐ ስግደት 30
8.2 የንስሐ ስግደት መቼ መቼ ይሰገዳል? 31
8.3 የንስሐ ስግድት ምን ምን እያልን እንሰገድ? 32

ክፍል ዘጠኝ 34

9.1 የቅዱሳን ስግደት 34
9.2 የጸጋ ስግደት 35
9.3 የጸጋ ስግደት መቼ መቼ እንሰገድ? 35
9.4 የጸጋን ስግደት ምን ምን እያልን እንሰገድ? 35

ክፍል አስር 37
10.1 የቅዱሳን ስግደት 37
10.2 ክብር ስግደት መቼ መቼ የእንሰግዳለን? 37
10.3 ክብር ስግደት ምን ምን እያልን እንሰገድ? 38

ክፍል አስራ አንድ 39
11.1 መቁጠሪያ 39
11.2 መቁጠሪያን እንዴት እንጠቀምበት? 40
11.3 መቁጠሪያን ለመጠቀም 41
11.4 ምን ምን እያልን እንቀጥቅጥ? 42

ክፍል አስራ ሁለት 43
12.1 የጸሎት ቤት መርሃ ግብር 43
12.2 የጸሎት ቤት ቅደም ተከተል 43
12.3 የመለኮተ ስሞች ትርጓሜ 46
12.4 ምግብ ስንበላ ምን ብለን እንባርክ? 46

ክፍል አስራ ሦስት 48
13.1 አጋንንትን ስለማሰር 48
13.2 አጋንንትን ለማሰር 49

ክፍል አስራ አራት 50
14.1 ቅዱስ ቁርባን አራት 50
14.2 የቅዱስ ቁርባን 7 ጥቅሞች አራት 50

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን

< በማለዳ ንቁ! >

(መዝሙረ ዳዊት ምዕ. 23)

1፤ እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።

2፤ በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።

3፤ ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።

4፤ በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።

5፤ በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።

6፤ ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

አባታችን ሆይ ፥ በሰማይ የምትኖር ፤ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህም ትምጣ ፍቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን። የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ፤ በደላችንንም ሁሉ ይቅር በለን፥ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል። አቤቱ፥ ወደ ፈተና አታግባን፤ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ። መንግሥት ያንተ ናትና፥ ኃይል፣ ክብር፣ ምስጋና እስከዘላለሙ ላንተ ይሁን።

አሜን።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፥ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፤ ሰላም እልሻለሁ። በሀሳብሽ ድንግል ነሽ፥ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። የአሸናፊ እግዚአብሔር እናት ሆይ፥ ሰላምታ ላንቺ ይገባል። ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤ የማኅጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። ጸጋን የመላሽ ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ፤ ልዑል እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና። ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን፣ ከአምላካችን፣ ከመድኃኒታችን፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድም ይቅርታንና ምሕረትን ትለሚኝልን ዘንድ፤ ኃጢአታችንንም ታሰርይልን ዘንድ ምስጋና ይሁን፥ አንድ አምላክ ለሚሆን፥ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

መግቢያ

ይህ < በማለዳ ንቁ! > የሚለው ዝግጅት በመጀመሪያ ዓላማና ራእይ የሚጠቁመው እንዴት በቤት ውስጥ አምልኮ ጠላትን መቋቋምና ማሸነፍ እንደሚቻል፤ ጌታችን ልዑል እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋም በመታገዝ የቃልኪዳኑን ኃይልና የተስፋውን እውነት በመግለጥ የመንግሥቱ ወራሾች የምንሆንበትን መሠረታዊ መንፈሳዊ መረጃ ነው።

አስተውሉ!

የሚለቀቀው ሁሉ የጽሁፍና የምስል መረጃ እንጂ ምግባር አይደለም። ምግባሩ የእናንተና የእናንተው ነው። እዚህ ላይ የተገለጹትን አካሄዶችና ተግባሮች ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ሕይወታችን አፈኗር ካደረስነው የሚወራ ብቻ ሳይሆን የሚታይ፣ የሚሰማ ብቻ ሳይሆን የሚገለጥ፣ የሚጸፍ ብቻ ሳይሆን የሚጨበጥ መንፈሳዊ በጎ ለውጥ አምጥተን በቅዱስ ሥጋና ደሙ በመታተም ለመንግሥተ ሰማያት የበቃን የምንሆንበት ሰማያዊ ጉዳይ ነው።

በዚህ ጽሁፍ የሚሰጡትም ሆነ እንደ ግል የማስተምራቸው መረጃዎችና ትምህርቶች በሙሉ በእውነተኛ አምልኮ ውስጥ የተገኙ ሙሉ በሙሉ መንፈሳዊ የሆኑ ተጨባጭ ናቸው። ማንኛውም ግለሰብ መረጃዎቹንና ትምህርቶቹን ወደ ምግባር በመቀየር ተጨባጭነቱን በሕይወቱ ማረጋገጥ ይችላል።

በቀጣይ < ክፉ መናፍስት እና የጥቃት አቅጣጫዎቻቸው > የሚል ዝግጅት ይኖረኛል።

<< ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል >> ወደ ቲቶ 2 ፤ 12-13

ክፍል - ፩

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም በመጀመሪያ ምን ከማድረግ እንጀምር ?

< የመጀመሪያውና ትልቁ የሁሉም ነገር መሰረት > ከአምላክ ጋር በፍቅር መጨባበጥ ነው!!

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

“ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።” ዮሐንስ 4፥8

ፍቅር በራሱ እግዚአብሔር ነው። መጀመሪያ ይህን ማወቅና ማመን ያስፈልጋል። በቃ ቃሉ እንደዚህ ነው የሚለው እግዚአብሔር ፍቅር ነውና!

የትኛውም እውነተኛ ፍቅር ከእግዚአብሔር ይጀምራል። በእግዚአብሔርም ይመራል። ከእግዚአብሔር ጋርም ይቀጥላል። የፍቅር መነሻም መድረሻም ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነው። የፍቅርን አባት፣ የሰላም አለቃ መድኃኒዓለም በራሱ ፍቅርነት እኛን ሲወደን ልክም አላበጀለትም። ወሰን በሌለው፣ ድንበር ባልያዘ ፍጹም ፍቅር እርሱ አፈቀረን።

"በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥37)

እርሱ አዶናይ ዓለምን ሁሉ በቃሉ ፈጥሮ ሳለ ዓለምን ጠቀለለና በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በኩል እግዚአብሔር ቃል በሥጋ ተዛመደን። በሥጋ እስኪወለድም፤ ከእኛም እንደ አንዱ ይሆን ዘንድ በጥልቅ ወደደን። ወደደን እናም አምላክ ሲሆን የሰው ልጅ ሆነና ከኛ ወገን ሆነ። አማኑኤል ሆነ በቃ።

"እግዚአብሔር አምላክም አለ። እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤" (ኦሪት ዘፍጥረት 3:22)

ተመልከቱ! ቃሉ እንዲህ ነው የሚለው።

"እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል።" 1 ዮሐንስ 4፥11

እግዚአብሔርን እንዲህ አድርጎ ከወደደን ይላል በቃ። በአባቱ አምላክ ነው። በእናቱ ወገናችን። ወገናችን እስኪሆን ድረስ ሰውን ወደደ ማለት ነው። ከዛ ደሞ እኛም ልንዋደድ ይገባናል ይላል። እግዚአብሔር በራሱ ፍቅር ነው። በእርሱ ፍቅር ደሞ እኛ በፍቅር እንኖራለን። በሰጠንም የሕያውነት እስትንፋሱ ውስጥ ማህተብ ሆና በተቀመጠች ፍቅሩ ሁሉንም እናፈቅራለን። ምንም አይነት ፍቅር ከእግዚአብሔር ፍቅር ካልጀመረ መድረሻ አይኖረውም። መድረሻ ቢኖረውም ፍፃሜው አያምርም።

እነሆም ታዲያ

የአምልኮ ኃይል ከእግዚአብሔር ፍቅር ካልተነሳ ዋጋ የለውም። እግዚአብሔርን ማፍቀር ለሁሉም መሠረቱና መነሻ ነው።ታላቂቱና መነሻይቱም የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው።

ሰማያዊ ቃሉ እንደዚህ ይነበባል።

"ኢየሱስም እንዲህ አለው። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም። ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።" የማቴዎስ ወንጌል 22፥37-40

ነብሱን የሰጠንን መድኃኔዓለምን ከእውነት ከልብ እናፍቅረው። ስንሰገድ በፍቅሩ ይሁን! ስንጸልይ በፍቅሩ ይሁን! ስንጾም በፍቅሩ ይሁን! ዲያቢሎስን ሸሽተን ሳይሆን መድኃኔዓለምን ሸተን ነው ፍቅርን መስጠት ያለብን!

ጸሎት፣ ስግደትና ጾም ስራ የሚሆንብን

አንደኛ - ለእግዚአብሔር የምንከፍለው ውለታ እንደሆነ አድርገን ስንቀበል

ሁለተኛ - ከእግዚአብሔር የሆነ መሻታችንን ለመሙላት ብቻ ስንጠቀምባቸው

ሶስተኛ - አጋንንትን ለማሳደድ ስንጠቀምበት ነው።

አምላክን በቀጥታ አፍቅረን ሲሆን ግን ለፍቅሩ እንሰግዳለን። ለፍቅሩ ነው የምንበረከከው። ለፍቅሩ እንጸልያለን። ይኸውላችሁ 'ከልብ ጸልዩ' የሚባለው እኮ እግዚአብሔርን አፍቅራችሁ ተመላለሱ ለማለት ነው። ሰይጣንም አጥብቆ የሚጠላውና የሚያሸንፈው <የፍቅር አምልኮ> ነው።

እስኪ እንፈትሽ። እግዚአብሔር እውን አፍቅረናል? አምልኮታችን ውስጥ ፍቅር አለ ወይ? ስንሰግድ ፍቅሩ አለ? ስንጾምና ስንጸልይስ? የእውነት እግዚአብሔርን እንወደዋለን? ወደ ውስጥ ወደ ልባችን እንፈትሽ።

ከሁሉ አስቀድመን ለፍቅር እንመላለስ። ፍቅርን ሳትይዙ አንድ ስንዝር አትጓዙም። ብትጎዙ እንኳ ዋጋ የላችሁም። ታውቃላችሁ ጎረቤቱን በክፉ እያየ የሚጸልይ አለ። አባቱን እናቱን አኩርፎ የሚሰግድ አለ። ጓደኛውን አስቀይሞ የሚጾም አለ።

"የጐመን ወጥ በፍቅር መብላት የሰባ ፍሪዳን ጥል ባለበት ዘንድ ከመብላት ይሻላል።"(መጽሐፈ ምሳሌ 15፥17)

ፍቅር የሌለው አምልኮና ጠባይ ውስጥ ክፋት ይደበቃል። ግራ ዘመምነት ተሰውሮ በኑሮአችን ውስጥ ኑሮ ሆኖ፣ እውነታ ያጣ፣ ከላዩ ብቻ የነጣ፤ ከውስጡ ግን የጠቆረን የአኗኗር ገጽታን እንድንላበስ ይሆናል። በዘመናችንም እርኩሳን መናፍስት ወደ ቤተ እግዚአብሔር በመቅረብና በዚያም ውስጥ በመመሸግ የአምልኮን ጉዞና ሕይወት ልምምድ የጀመሩት በዚህ ፍቅር ከሌለበት አምልኮ ውስጥ ስፍራና ቦታ ስላገኙ ነው።

ግን ይኸውላችሁ ቅዱስ ቃሉ እንዲህ ይላል።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5፥1 "እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥ 2 ክርስቶስ ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።"

የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ንጹህ ፍቅር ለማወቅና በውስጡም ለመኖር አስቀድማችሁ አስቡ። መድኃኔዓለምን አጠገባችሁ እንዳለ አባት ከማፍቀር ሁሉን ጀምሩ። ከዚህ ካልተነሳችሁ መድረሻ የላችሁም። ፍቅር ከሁሉ ይበልጣል። ፍቅር ከሁሉ ይቀድማል። ስለዚህ መመሪያ አንድ፤ ትምህርት አንድ ስንል ፍቅር ብለን እንጀምራለን።

(1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ምዕ. 13)

1፤ በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ።

2፤ ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።

3፤ ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።

4፤ ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤

5፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤

6፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤

7፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።

8፤ ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።

9፤ ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤

10፤ ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል።

11፤ ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፥ እንደ ልጅም አስብ ነበር፥ እንደ ልጅም እቈጥር ነበር፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ።

12፤ ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።

13፤ እንዲህም ከሆነ፥ እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።

ክፍል ፪

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ ?

< የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ> አፌሶን 6፥10-18

በእውነተኛ ክርስትና ውስጥ ዘመንን ለማሳለፍ፣ በአፍ ሳይሆን በምግባር የተገለጠ ሰማያዊ አኗኗርን ለመገንባትና እርኩሳንን መናፍስትን በእግዚአብሔር ክንድ ጥሎ በጸጋውና በኃይለ መለኮቱ በኩል ለመሰለፍ የመጀመሪያው እርምጃችን መድኃኒዓለምን ከልብ ማፍቀር ነው ብለናል።

"የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፥ ለሚያደርጓትም ሁሉ ደኅና ማስተዋል አላቸው፤ ምስጋናውም ለዘላለም ይኖራል። " (መዝሙረ ዳዊት 111፥10)

እግዚአብሔርን የምንፈራው አስቀድሞ ስናፈቅረው ነው። ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር ካልተነሳ ባዶ ነው። ከንቱ ነው። አምልኮ ውስጥ እግዚአብሔርን ማፍቅር ከሌለ ዋጋ የለውም። እግዚአብሔርን ማፍቀር ለሁሉም መሠረቱ ነው።

"ኢየሱስም እንዲህ አለው። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም። ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።" የማቴዎስ ወንጌል 22:37-40

ክርስትናችንን ከእግዚአብሔር ፍቅር ካስጀመርን በኃላ አስከትለን ምን እናድርግ ? ይሕንን የሚመልስልን የመጽሐፍ ቅዱስ ምሪት እንመልከት።

"በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያቢሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከስልጣናት ጋር ከዚህ ጨለማ ዓለም ገዥዎች ጋር በሰማይ ስፍራ ከነበራቸው ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉ ቀን ለመቃወም፣ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፣ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፣ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፣ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉዎች ፍላፃዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነት ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ። "

ቃል በቃል ብታነቡት እያንዳንዷ ቃላት ላይ እውነቱን መጽሐፍ ቅዱስ አስቀምጦታል። "የዲያቢሎስን ሽንገላ እንድትቃወሙ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ልበሱ" ይላል።

2.1. የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ የሚባሉት ምንድን ናቸው?

ማርቆስ 12:17

ኢየሱስም፣ “የቄሳርን ለቄሳር፣ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ” አላቸው። እነርሱም በእርሱ ተደነቁ።

የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ የሚባለው ከእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ ነው። ከእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ ደሞ እውነተኛ በሕይወቱ የተጨበጠና ለሌላው መድረስ የሚችልን ክርስትና የያዘውን ሁሉ ነው። ይኽንን የክርስትና መንገድ ደግሞ በሰማያዊ ኃይልና ሞገስ ጠብቃ፣ በእውነተኛ የታሪክ መሠረትና የቃልኪዳን ምሪት ገንብታ፣ በአምላክም ጸጋና የረድኤት ሥልጣን ታግዛ፣ በቅዱሳንም የጽድቅ መንፈስ ምሳሌነት ተመርታ፣ በመስዋትነትና በጽናትም ጽንታ የቆመች ደግሞ አንድ የእውነት ሃይማኖት ብቻና ብቻ ናት።

(ወደ ኤፌሶን ሰዎች ምዕ. 4)

5፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤

6፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።

ሃይማኖት ናት የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ።

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውን መንገድ ጠይቁ፤ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ፤ በእርስዋም ላይ ሂዱ፤ ለነፍሳችሁ እረፍት ታገኛላችሁ። እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ።" ትንቢተ ኤርምያስ ምዕ 6፥16

የቀደመቺው መንገድ አንዲቷ ሃይማኖት ናት። መልካሚቱ መንገድ ሃይማኖት ናት። ለነፍስ እረፍት የምናገኝባት ሃይማኖት ናት።

ስለዚህም

< ንቁ በሃይማኖት ቁሙ ጎልምሱ ጠንክሩ በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።> 1ኛ ቆሮ፣16፣13

2.2. በሃይማኖት መቆም ምን ማለት ነው?

በቀጥተኛ ገለጻና አነጋገር በሃይማኖት መቆም ማለት ዘወትር በመንፈሳዊ ልምምድ በተግባር መመላለስ ማለት ነው።

2.3. መንፈሳዊ ልምምድ ምን ምንድን ናቸው?

በቤት ውስጥ የጸሎት ቦታ፣ ስፍራና ጊዜ አበጅቶ

✔ የዘወትር የአምልኮ ስግደት

✔ የዘወትር ጸሎት

✔ ጾም

✔ ቁርባን

✔ ንስሐ

✔ አስራት በኩራት

✔ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት

✔ ከክፋት መሸሸና መቃወም

ዋነኛ የመንፈሳዊ ልምምድ ናቸው።

በቀጣይ ክፍሎች ጸሎት ቤትን ከማዘጋጀት አስጀምረን ስለ እያንዳንዷ መንፈሳዊ ልምምድ በመጽሐፍ ቅዱስ ምሪት መሠረት እንመለከታለን።

(ወደ ኤፌሶን ሰዎች ምዕ. 4)

1፤ እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤

2፤ በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም፤ እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፤

3፤ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።

4፤ በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤

5፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤

6፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።

7፤ ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን።

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ ?

ክርስትና ሃሳብ አይደለም። ክርስትና እቅድ አይደለም። ክርስትና ልማድ አይደለም። ክርስትና ባህልም አይደለም። ክርስትናን ጊዜ አይገድብም። ነጠላ ሲወልቅ አብሮ የሚወልቅ አይደለም። ክርስትና የዕለት ተዕለት ኑሮ ነው። ክርስትና ዘወትር ክርስቶስን መከተል ነው። ቃሉን ተመልከቱ።

"ለሁሉም እንዲህ አላቸው። በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።" (የሉቃስ ወንጌል 9፥23)

ክርስትና የዘወትር ጉዞ ነው። በእያንዳንዷ የሕይወታችን ቅጽበት መኖር የሚገባው መንገድ ነው። ክርስትና ዛሬ ጀምረን ነገ የምንተወው ብልጭታ አይደለም። ዕለት ዕለት ይከተለኝ ነው እኮ የመድኃኒዓለም ሰማያዊ ድምጽ ያለው።

3.1 ታዲያ በክርስትና ዕለት ዕለት እንዴት መኖር እንችላለን?

ለዚህ ቀጥተኛውና ግልጹ ምላሽ ዘወትር በምንገኝበት ቦታ ላይ ለአምላካችን አዶናይ እግዚአብሔር ራሳችንን በፍቅር አምልኮ በማስገዛት አካሄዳችንን በመለኮቱ ምሪት ላይ መዘርጋት የሚለው ይሆናል።

3.2 ይሕንን ለማድረግ ምን ከማድረግ እንጀምር?

" እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን። " (መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 24፥15)

አብዛኞቻችን በብዛት ሰፊ ጊዜያችንን የምናሳልፈው፣ የምናርፈው፣ ኑሮአችንን የምንመራው፣ ቤተሰብ የምንመሠርተውና ወዘተ.. ከቤታችን ሆነን ነው። ስለዚህ ክርስትና ከቤት ይጀምራል። ብዙዎቻችን ክርስትናን የምናውቀው ቤተክርስቲያን ብቻ ነው። ቤተክርስቲያን መቀደሻችን፣ መባረኪያችን፣ ቃሉን መስሚያችን፣ በጋራም ማመስገኛችን፣ ሥጋና ደሙን መቀበያችን፣ በጽላቱም መባረኪያችን፣ ማስቀደሻችን ናት። ሁሉም ክርስቲያን ሊባል የጣቶች ቁጥር የቀረው በሚመስል ደረጃ ከቤተክርስቲያን ሲወጣ ክርስትናውም በዛው ይወጣል።

ክርስትና የዕለት ተዕለት ምግባር ከሆነ ግን ዕለት ዕለት ከምንገኝበት ቤት የሚጀምር አምልኮ ያስፈልገናል። ምክንያቱም ፡

❖ አንደኛ - ዘወትር የሰላም ኑሮን እያገኘን እንሄዳለን። ሰላም የሚጀምረው ከውስጠኛ ክፍላችን ነው። እነሆም ዘወትር በቤታችን የጸሎት ቦታና ጊዜ ካለን የሰላም አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤታችን ይገባልና ሰላማችን እየበዛ ይሄዳል።

❖ ሁለተኛ - ክፉ መናፍስታንን በየዕለቱ እየተቃወምን እንከላከላቸዋለን። ይሕም ማለት፡

❶• ከውስጥ በኩል ያደፈጠ ጠላት እየተዳከመ ይመጣል።

❷• ቤታችን ውስጥ አስቀድመው የነበሩና ያሉ መናፍስቶች ከቤታችን ለመራቅ ይገደዳሉ።

❸• የቤተሳባችን አባላት ላይ ያደፈጠ ጠላት አምልኮታችን ይበጠብጠዋል። ከበረታንም ይጋለጣል።

❹• ሰፈራችን አቅራቢያ የሚልከሰከሱ እንደ የዛር፣ የመናፍቅ፣ የቡዳና ወዘተ.. መናፍስት እይታቸው ይደበዝዛል። ከእኛ መራቅና መሸሽ ይጀምራሉ።

❺• ከስራ ቦታ ከትምህርት ቤት አስቀድመው አልፈው ወጥመድ የሚያዘጋጁ እንደ ዓይነጥላ ያሉ መናፍስት ግብራቸው ይከሸፋል።

❻• በመንገዳችንና በጉዛችን ላይ የሚኖሩ የሰላቢ፣ የቡዳ፣ የቁራኛና የሱሉስ ዝውውር መናፍስት በሙሉ ከለላ ስላለን ሊጠጉን አይቻላቸውም።

❖ ሶስተኛ - ራእይና የእግዚአብሔር መልእክትን ለሕይወታችን ምሪት ይሆነን ዘንድ በቃልኪዳኑና በተስፋው ኃይል በኩል እናገኛለን።

❖ አራተኛ - 'የነገን አንተ ታውቃለህ 'ብለን ስንተኛ የነገውን ለእግዚአብሔር ሰጥተናልና ሳንጨነቅ የምንውልበትን የሕይወት ዕድል ከተከፈቱ መልካም አጋጣሚዎች ጋራ እናገኛለን

3.3 ስለዚህ የጸሎት ቤት እንዴት እናዘጋጅ?

የጸሎት ቤት በመኖሪያ ቤታችን ውስጥ የምንገነባው ትንሽዬ መቅደስ ማለት ነው። ጸሎት ቤታችንንና የቤተክርስቲያናችንን ቅድስት ቤተመቅደስ ምን እንደሚያገናኛቸው በቀጣዩ ክፍል ለብቻው እንመለከታለን።

አንደኛ ✔ ቤታችንን በንስሐ አባታችን ወይንም በካህን ሁሉንም ያለውን ክፍል ጸበል ማስረጨትና ማስባረክ።

ምክንያቱም - በቤታችን ውስጥ የሚገኙ እርኩሳን መናፍስትን ያሸሻልና። የሚባርክል ካህን ካላገኘን ግን፤ እስከምናገኝ እራሳችን ጸበልን አምጥተን በስሙ ባርከን መርጨት፤ መርጨት የማንችል በጨርቅ በመንከር የጸሎት ስዕለ አድንኖዎቹን የምንለጥፍበትን ግድግዳ እንጠርጋለን።

ሁለተኛ ✔ የምሥራቁን አቅጣጫ የተከተለ የግድግዳችን ስፍራ ለጸሎት ቦታ የተመረጠው ነው።

ምክንያቱም - በቅዱስ ቃሉ "በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ።" (የዮሐንስ ወንጌል 9፥5) ጌታችን ብሎናል። ብርሃነቱን በጸሀይ እንወክላለን። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ብሏልና። የጸሀይ መውጫ ደግሞ ምሥራቅ ናት። እመቤታችንም አማናዊት ምሥራቅ ናት።

"ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ፥ እነሆ፥ ሰብአ ሰገል። የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ።" (የማቴዎስ ወንጌል 2:1-2)

ሰብአ ሰገል የክርስቶስን መንገድ ያገኙት የምሥራቁን መንገድ ተከትለው ነው። እኛም እንዲሁ በጸሎት ቤታችን የክርስቶስን መንገድ እንፈልጋለንና ወደ ምሥራቅ ዞረን የፍቅር አምልኮን በቤታችን እንሰዋለን።

ሦስተኛ ✔ በመቀጠል ያሰናዳነው ግድግዳ ላይ በጥሩ ፍሬም የተሰሩና በጽዳት የተጠበቁ፣ የተባረኩ፣ ቅባዕ ቅዱስ የተቀቡ፣ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሥርአትን የጠበቁ ስዕለ አድኖዎችን በሚገባቸው ሥርአትና ደንብ እንደረድራለን።

ምክንያቱም ፡ ስዕለ አድኖዎች እንዲሁ የመገለጫ ምስሎች የሚሆኑት እንዲሁ ባገኘንበት ለጥፈን ለጌጥና ማድመቂያ ስንጠቀማቸው ነው። አባቶቻችን ግን ስዕለ አድኖዎችን ሲያዘጋጁ ለጸሎት እንዲውሉ፣ ኃይለ መንፈስ ቅዱስ እንዲያርፍባቸውና የተጠቀመባቸውም ሁሉ ከዚሁ በረከት እንዲካፈል በማለት ነው። እኛም ለዚሁ አገልግሎት ስንጠቀማቸው የክርሰትናችን ጉልበት ነው።

አደራደራቸው የሚከተለው ነው።

በመቆም ልክ በግንባር ትይዩ - የአጋእዝተ ዓለም ሥላሴን። በዛው መስመር በጎን በጎን የመድኃኒዓለምን ምስሎች

ምክንያት፡ የአብርሃሙ ሦስቱ ሥላሴዎች ምስልን ካስተዋላችሁ ዓለምን የያዙ ሥላሴዎችን ያሳያል። አጋእዝተ ዓለም ሥላሴም ስንል ከሁሉ በላይ ያሉ፣ ዓለምን የፈጠሩና ዓለምንም የሚገዙ መሆናቸውን ስናመለክት ከፍ አድርገን በመቆም ግንባር ልክ እንሰቅላለን።

መድኃኒዓለምም ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ወልድ እግዚአብሔር ነውና በምድር የተመላለሰበትን ወቅት የሚያሳዩ ምስሎቹ ከፍ ተደርገው በጎን በጎኑ ይሰቀላሉ።

በመንበርከክ ልክ ከግንባር ትይዩ - የእመቤታችን ከተወደደው ልጇ ጋር። በግራ የቅዱስ ሚካኤል። በቀኝ የቅዱስ ገብርኤል።

ምክንያት፡ ከፍጡራን ተለይቶ በሚስጥረ ሥጋዌ ሰውነትን የተካፈለባት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከሥላሴዎች በታች ከፍጡራን ግን በላይ ናትና ይሄንኑ እናሳያለን። ግራና ቀኝ ሁለቱ ኃያል ሊቃነ መልአክት ከእመቤታችን አይለዩምና ይኽንኑ እናሳያለን።

ከበታች - የቅዱሳንን ሁሉ ምስል በየዘርፋቸው እናደርጋለን።

ምክንያት: "ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፥ ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ።"(መዝሙረ ዳዊት 8፥9) እንዲል ልዑል እግዚአብሔር፤ ከመረጣቸው ቅዱሳን የቃልኪዳን ጸጋና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንካፈል ዘንድ ምስላቸውን መጠቀም የሕይወት በረከትና መንፈሳዊ አጋር የማግኛ የክርስቲያን ትልቅ ስጦታ ነው።



ስዕለ አድኖዎቹን በእንዲህ መልክ ከደረደርን በኃላ የሚያስፈልጉንን የጸሎት ቤት ንብረቶች እናዘጋጃለን።

እነርሱም በዋናነት ፡

- ✓ መስገጃ ምንጣፍ
- ✓ ምንጣፉ ላይ የሚደረደሩ የጸሎት መጽሐፍት። መቅረት የሌለበት 'መዝገበ ጸሎት እና አርጋኖን' ናቸው። ቢቻለን ሁሉን የጸሎት መጽሐፍ ብንጠቀም ጥሩ ነበረ። ግን የምንችለው ያህል ቅዱስ የጸሎት መጽሐፍ እናዘጋጃለን።
- ✓ የተባረከና ቅባዕ ቅዱስ የተቀባ መቁጠሪያ
- ✓ ጠበል፣ እምነት፣ ቅባዕ ዘይት፣ ሜሮን
- ✓ የተባረከ የመቅደስ እጣንና ማጤሻው፤ ሻማና መቅረዝ ሌሎችንም ቅድሳን ንበረቶች እናዘጋጃለን።

የተያያዙ መረጃዎች:

✔ ስንጸልይ ወደ ስዕለ አድኖቹ የመጽሐፍ መግለጫ ያህል ርቀት ጠጋ ብለን ነው።

ምክንያት: ከተባረኩትና በጥንቃቄ ከተያዙት ስዕለ አድኖዎች የሚወጣው መንፈሳዊ ኃይል በጸሎትና ስግደት ወቅት ከውስጥ ያደፈጠን ጠላት ያቃጥላልና ነው።

✔ የተባረከው እጣንና ሻማ በየሰንበቱ ክብረ በዓሉ እንጠቀማቸዋለን።

ምክንያት: "የእግዚአብሔር ስም የጸና ግምብ ነው፤ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል። " (መጽሐፈ ምሳሌ 18፥10)

ስለዚህ በእግዚአብሔር ስሙ የተባረከው ሁሉ የጸናውና የተባረከው ነውና በስሙ ከመቅደሱ ተባርኮ የመጣው እጣን በጤሰ ጊዜ ክፉ ኃይላት ይቅበዘበዛሉ፤ ይሸሹማል።

✔ ጠበሉም ሆነ የትኛውንም የጸሎት ቤት ክፍል ለሌላ አገልግሎት መጠቀም አይፈቀድም።

ምክንያት: "እርሱም። እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው።" (የሉቃስ ወንጌል 20፥25)

ታዲያም የተባረኩትና በስሙ የተቀደሱት ንበረቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ናቸው ለእግዚአብሔር የሚውል አገልግሎት ብቻ ላይ ይውላሉ። ለሌላ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ውጪ በተጠቀምናቸውና እንዳገኘንም የምንጥላቸው ከሆነ መንፈሳዊ ኃያላቸውን እንጥልባቸዋለን።

ክፍል - ፭

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ ?

4.1 የጸሎት መርሃ ግብርና ሰዓታት

በመሠረቱ የሰው ልጅ 24 ሰዓታቱን ሁሉ ጸሎት ማድረስ ይችላል። በዚህ ሰዓት አትጸልዩ የሚል ገደብ ክርስትና የለውም። ነገር ግን በዓለምምም ስንኖር የሥጋ ኑሮአችን የየቀኑን ሰዓታት በተለያየ ምክንያት ይይዘዋልና ቤተክርስቲያናችን ለምዕመናኖቿ የጸሎት መርሃ ግብርና ሰዓታትን በሰማያዊ ምክንያት ቀርጻ አሰናድታ አቀርባለች። መነሻ ምሪቷም እንዲህ የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይሆናል።

"ስለ ጽድቅህ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ።" (መዝሙረ ዳዊት 119፥164)

የሚለውን የልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትን ቃል ስንመለከት በቀን 7 ጊዜ የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እንዲያመልክ መታዘዙን ያመለክታል።

ይኸውም በቤተክርስቲያናችን ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት በመባል ይታወቃሉ።

ይኸውም ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት የሚባሉት እና የሚጸለዩ ጸሎቶች፦

❶• ነግሕ ፦ ጠዋት 11:00 ሰዓት ወይንም (በፈረንጆቹ 5:00 AM)

የሚጸለዩት ጸሎቶች - የዘወትር ጸሎት፣ ውዳሴ ማርያም፣ ይዌድስዋ መላእክት፣ ሠይፈ ሥላሴ፣ ሠይፈ መለኮት

- ጠዋት 11:00 አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን አምላክን በፀሎት የሚያመሰግንበት ምክንያት (ሚስጥር)

1 እግዚአብሔር አምላክ ሌሊቱንና ጨለማውን አሳልፎ ብርሀን እንድናይ ስላበቃን በዚህ ሰአት እግዚአብሔር አምላካችንን እንድናመሰግን ታዝዝዋል አንድም በዚህ ሰአት ጌታችን ለክስ ከጲላጦ ፊት ቆሞ የተወቀሰበት ሰአት ስለሆነ አንድም በዚ ሰአት አባታችን አዳም ያልተፈቀደለትን እፅ በልቶ ከገነት የተባረረበት ሰአት ስለሆነ ነው አንድ ክርስቲያን ይህን ሁሉ እያሰበ ወደ አምላኩ እንዲፀልይ ታዝዋል

❷• ሦስት ሰዓት ጠዋት 3:00 ሰዓት ወይንም (በፈረንጆቹ 9:00 AM)

የሚጸለዩት ጸሎቶች - መዝሙረ ዳዊት፣ መልክአ ገብርኤል

- ሰልቱ ሰአት ከጠዋቱ 3 ሰአት አንድ ክርስቲያን እንዲፀልይ የታዘዘበት ምክንያት (ሚስጥር)

1 በዚህ ሰአት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብስራተ ገብርኤልን የሰማችበት ሰአት ስለሆነ ነው አንድም በዚህ ሰአት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችንን የፀነሰችበት ሰአት ስለሆነ ነው አንድም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጲላጦስ ፊት ቀርቦ የተገረፈበት ሰአት ስለሆነ፤ እያንዳንዱ ክርስቲያን ይሔንን የመሳሰሉ ሁሉ እያሰበ እግዚአብሔር አምላኩን እንዲያመሰግን ታዝዋል

❸• ስድስት ሰዓት (ጊዜ ቀትር) 6:00 ሰዓት ወይንም (12:00 PM በፈረንጆች)

የሚጸለዩት ጸሎቶች - መልክአ ሚካኤል፣ መልክአ ሥላሴ

- 6:00 አንድ ክርስቱያን እኩለ ቀን (ከ ቀኑ 6 ሰአት) ሲሆን እንዲፀልይ የታዘዘበት ምክንያት ወይም (ሚስጥር)

1 ጌታችን በቀራኔዎ አደባባይ በመስቀል ተሰቅሎበታልና አንድም ልብሱን ተገፎበታል አንድም ሳዶር አላዶር ዳናት ሮዳስ በተባሉ ችንካሮች ተቸንክሮበታልና በሌላም ቅዱስ ሚካኤል በዚህ ሰዓት ክፉ መናፍስትን አሸንፎ ጥሎበታልና አንድ ክርስቲያን ይህን ሁሉ እያሰበ በዚህ ሰአት እንዲፀልይ ታዞበታል

❹• ዘጠኝ ሰዓት ከሰዓት 9:00 ሰዓት ወይንም (3:00 PM በፈረንጆች)

የሚጸለዩት ጸሎቶች - መልክአ መድኃኔዓለም፣ መልክአ ዑራኤል

- ተስአተ ከ ቀኑ 9:00 ሰአት ሲሆን አንድ ክርስቲያን የሚፀልይበት ምክንያት (ሚስጥር)

1 አይሁዶች ጌታችን መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መራራ ሐሞት አጠጥተውበታል አንድም ቅድስት ነፍሱን ከ ክቡር ስጋው የለየበት ሰአት ነውና አንድም በመስቀል እንዳለ 7 ቱን አፅርሀ መስቀል የተናገረበትና ቅዱስ

ዑራኤል ከጎኑ ውጋት ደም በዋንጫ ቀድቶ ዓለም ላይ የረጨበትም ነውና አንድ በዚህ ሰአት ይህንን እያሰበ እንዲፀልይ ታዝዋል

❺• ሰርክ ፦ አስራ አንድ ሰዓት 11:00 ወይንም (5:00 PM በፈረንጆች)

የሚጸለዩት ጸሎቶች - ውዳሴ ማርያም፣ የጎሊና ጸሎት፣ የምጎላ ጸሎት

- የሰርክ ሰአት ከቀኑ 11:00 ሰአት አንድ ክርስቲያን እንዲፀልይበት የታዘዘበት ምክንያት ወይም (ሚስጥር)

1 ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ከርሰ መቃብር የወረደበት ሰአት ስለሆነ አንድም ቀኑን በሰላም አሳልፎ ወደ ምሽት በሰላም ያደረሰን አምላክ ምስጋ ስለሚገባው ነው ይህንን የመሳሰሉ ሁሉ ሕዝበ ክርስቲያን እንዲያስቡ ታዘዋል

❻• ጸለፀተ ንዋም ማታ 3:00 ሰዓት ወይንም (9:00 PM በፈረንጆች)

የሚጸለዩት ጸሎቶች - የዘወትር ጸሎት፣ አርጋኖን

- ከምሽቱ 3 ሰአት በዚህ ሰአት አንድ ክርስቲያን እንዲያመሰግን የታዘዘበት ምክንያት (ሚስጥር)

1 በዚህ ሰአት እራሱ ጌታችን መድሀኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ስርአተ ፀሎት አሳይቶበታል አንድም በዚህ ሰአት ጌታችንን አይሁድ በይሁዳ ጠቁዋሚነት ተረበርበው የያዙበት ሰአት ስለሆነ ነው አንድም በዚህ ሰአት አንድ ክርስቲያን ከመተኛቱ በፊት በሰላም ያዋለንንና ያስመሸንን አምላክ አመስግኖ መተኛት አለበት ይህን ሁሉ እያሰበ እንዲፀልይ ታዝዋል

❼• እኩለ ለሊት 6:00 ሰዓት ወይንም (12:00 AM በፈረንጆች)

የሚጸለዩት ጸሎቶች - መዝሙረ ዳዊት

- መንፈቀ ሌሊት ከሌሊቱ 6 ሰአት በዚህ ሰአት አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔር አምላኩን እንዲያመሰግንበት የታዘዘበት ምክንያት (ሚስጥር)

1 በዚህ ሰአት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶበታልና ነው አንድም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን ድል አድርጎበታልና(ተነስቶበታል) በመዝሙረ ዳዊት አመሰግንህ ዘንድ በመንፈቀ ሌሊት እነሳለው ባለውም መሠረት።

በቃል መያዝ የሚገባቸው ጸሎቶች

አስቀድሞ በተለዋወጥነው መረጃ መሠረት የጸሎት ቤታችንን በሚገባ የፍቅርና የክብር ልክ በጥንቃቄ ካዘጋጀን በኃላ የሚቀጥለው ክፍል እንዴት እንጠቀምበት የሚለው ይሆናል።

በዘወትርም የመንፈሳዊ የጸሎት ቤት ምግባራት ውስጥ ስግደት፣ ጸሎትና መቁጠሪያ ሳይቋረጡ፤ ጸሎት ቤት በገባን ቁጥር የምንተገብራቸው የዕለት ዕለት ልምምዶች ናቸው። በምንም መልኩ ዘወትር አይቋረጡም!!

በቃል ልንይዛቸው የሚገቡ ጸሎቶችን ከስር ታገኙታላችሁ።

መዝሙር 22 (23)

1. እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፣ የሚያሳጣኝም የለም፡

2. በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል።

3. ነፍሴን መለሳት፣ ስለስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።

4. በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብኼድ አንተ ከኔ ጋር ነኽና፣ክፉን አልፈራም፤ በትርኽና ምርኩዝኽ እነርሱ ያጸናኑኛል።

5. በፊቴ ገበታን አዘጋጀኽልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባኽ፣ ጽዋዬም የተረፈ ነው።

6. ቸርነትኽና ምሕረትኽ በሕይወቴ ዘመንኹሉ ይከተሉኛል፣ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘለዓለም እኖራለኹ።

መዝሙር 90 (91)

1. በልዑል መጠጊያ የሚኖር ኹሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል።

2. እግዚአብሔርን፦አንተ መታመኛዬ ነኽ እለዋለኹ፤ አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው፣ እታመናለኹ።

3. እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንኻልና።

4. በላባዎቹ ይጋርድኻል፣ በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ፤ እውነት እንደ ካባ ይከብብኻል፡

5. ከሌሊት ግርማ፣በቀን ከሚበርር ፍላጻ፣

6. በጨለማ ከሚኼድ ክፉ ነገር፣ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም።

7. በአጠገብኽ ሺሕ በቀኝኽም ዐሥር ሺሕ ይወድቃሉ፣ ወደ አንተ ግን አይቀርብም።

8.በዓይኖችኽ ብቻ ትመለከታለኽ፣ የኃጥኣንንም ብድራት ታያለኽ።

9. አቤቱ፣አንተ ተስፋዬ ነህና፤ ልዑልን መጠጊያኽ አደረግኽ።

10. ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፣ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም።

11. በመንገድኽ ይጠብቁኽ ዘንድ መላእክቱን ስለአንተ ያዝዛቸዋልና፤

12. እግሮኽም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡኻል።

13.በተኩላና በእባብ ላይ ትጫማለኽ፣አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለኽ።

14.በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለኹ፣ስሜንም አውቆአልና እጋርደዋለኹ።

15. ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፣ በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ እኾናለኹ፣ አድነዋለኹ አከብረውማለኹ።

16.ረጅምን ዕድሜ አጠግበዋለኹ፣ ማዳኔንም አሳየዋለኹ።

መዝሙር 50 (51)

1.አቤቱ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ።እንደ ምሕረትኽም ብዛት መተላለፌን ደምስስ፡

2.ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፣ ከኃጢአቴም አንጻኝ። እኔ መተላለፌን አውቃለኹና፡

3.ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነው።

4.አንተን ብቻ በደልኹ በፊትህም ክፋትን አደረግሁ፣ በነገርኽ ትጸድቅ ዘንድ በፍርድኽም ንጹሕ ትሆን ዘንድ፡

5. እነሆ በዓመፃ ተፀነስኹ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።

6.እነሆ እውነትን ወደድኽ፣ የማይታይ ስውር ጥበብም አስታወቅኸኝ።

7.በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ፣ እጸበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ።

8.ሐሤትና ደስታን አሰማኝ፣ የሰበርኻቸውም አጥንቶቼ ደስ ይላቸዋል።

9.ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ፣ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ።

10. አቤቱ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ፣ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።

11.ከፊትህ አትጣለኝ፣ ቅዱስ መንፈስህንም አትውሰድብኝ።

12.የማዳንኽን ደስታ ስጠኝ፣ በእሽታ መንፈስም ደግፈኝ።

13.ለሕግ ተላላፊዎች መንገድኽን አስተምራለሁ፣ ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ።

14. የመድኃኒቴ አምላክ እግዚአብሔር ኾይ ከደም አድነኝ፣

15. አንደበቴም በአንተ ጽድቅ በአንተ ጽደቅ ትደሰታለች። አፌ ምስጋናኽን ይናገር ዘንድ አቤቱ ከንፈሮቼን ክፈት።

16. መሥዋዕትን ብትወድስ በሰጠሁህ ነበር፣ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ደስ አያሰኝህም፡

17. የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነውና። የተሰበረውን የተናቀውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም፣

18. አቤቱ በውዴታኽ ጽዮንን አሰማምራት፣፣ የኢየሩሳሌምን ቅጽሮች ሥራ።

19.የጽድቁን መሥዋዕት፣ መባውንም፡ የሚቃጠለውንም መሥዋዕት በወደድኽ ጊዜ፣ ያን ጊዜ በመሠዊያኽ ላይ ፍሪዶች ይሠዋሉ።

መዝሙር 23

1. አቤቱ፥ ወደ አንተ ነፍሴን አነሣለሁ።

2. አምላኬ፥ አንተን ታመንሁ፤ አልፈር፣ጠላቶቼ በእኔ አይሣቁብኝ።

3. አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም፤ በከንቱ የሚገበዙ ያፍራሉ።

4.አቤቱ፥ መንገድህን አመልክተኝ፥ ፍለጋህንም አስተምረኝ።

5. አንተ የመድኃኒቴ አምላክ ነህና በእውነትህ ምራኝ፥ አስተምረኝም፤ ቀኑን ሁሉ አንተን ተስፋ አድርጌአለሁ።

6.አቤቱ፥ ምሕረትህንና ቸርነትህን አስብ፥ ከጥንት ጀምሮ ናቸውና።

7.የልጅነቴን ኃጢአትና መተላለፍ አታስብብኝ፤ አቤቱ፥ ስለ ቸርነትህ ብዛት እንደ ምሕረትህ አስበኝ።

8. እግዚአብሔር ቸር ቅንም ነው፤ ስለዚህ ኃጢአተኞችን በመንገድ ይመራቸዋል።

9. ገሮችን በፍርድ ይመራል፥ ለገሮችም መንገድን ያስተምራቸዋል።

10. የእግዚአብሔር መንገድ ሁሉ ቸርነትና እውነት ነው። ቃል ኪዳኑንና ምስክሩን ለሚጠብቁ።

11. አቤቱ፥ ኃጢአቴ እጅግ ነውና ስለ ስምህ ይቅር በለኝ።

12. እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ማን ነው? በሚመርጠው መንገድ ያስተምረዋል።

13. ነፍሱ በመልካም ታድራለች፥ ዘሩም ምድርን ይወርሳል።

14. እግዚአብሔር ለሚፈሩት ኃይላቸው ነው፥ ቃል ኪዳኑንም ያስታውቃቸዋል።

15. እርሱ እግሮቼን ከወጥመድ ያወጣቸዋልና ዓይኖቼ ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር ናቸው።

16. እኔ ብቻዬንና ችግረኛ ነኝና ፊትህን ወደ እኔ አድርግ ማረኝም።

17. የልቤ ችግር ብዙ ነው፤ ከጭንቀቴ አውጣኝ።

18. ድካሜንና መከራዬን እይ፥ ኃጢአቴንም ሁሉ ይቅር በለኝ።

19. ጠላቶቼ እንደ በዙ እይ፥ የግፍም ጥል ጠልተውኛል።

20. ነፍሴን ጠብቅና አድነኝ፤ አንተን ታምኛለሁና አልፈር።

21. አንተን ተስፋ አድርጌአለሁና የውሃትና ቅንነት ይጠብቁኝ።

22.አቤቱ፥ ኢትዮጵያን (እስራኤልን) ከመከራው ሁሉ አድነው።

መዝሙር 40 (41)

1. ለችግረኛና ለምስኪኑ የሚያስብ ምስጉን ነው፣ እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድነዋል።

2. እግዚአብሔር ይጠብቀዋል ሕያውም ያደርገዋል፡ ፡በምድር ላይም ያስመሰግነዋል፡ በጠላቶቹም እጅ አሳልፎ አይጥለውም።

3. እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ሳለ ይረዳዋል፣ ምኝታውን ሁሉ በሕመሙ ያነጥፍለታል።

4. አቤቱ እኔንስ ማረኝ፣አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት እላለኹ።

5 ጸላቶቼም በላዬ ክፉ ይናገራሉ። መቼ ይሞታል ስሙስ መቼ ይጠፋል ይላሉ፣

6. እኔን ለማየትየተገባው ቢኾን ከንቱን ይናገራል።ልቡ ኃጢአትን ይሰበስባል፣ ወደ ሜዳም ይወጣል ይናገራልም።

7. በላዬ በመመካከር ጸላቶቼ ሁሉ ይንሾካሸኩብኛል። በኔ ላይም ክፋትን ያስባሉ፡

8. ክፉ ነገር መጣበት ተኝቶአል፣ ከእንግዲህ ወዲህ አይነሣም፡ ይላሉ።

9. ደግሞ የሰላሜ ሰው የታመንሁበት፣ እንጀራዬን የበላ በኔ ላይ ተረከዙን አነሣ።

10. አንተ ግን አቤቱ ማረኝ፣ እመልስላቸውም ዘንድ አስነሣኝ።

11. ጸላቴ እልል ይልብኝ ዘንድ አልወድም። ስለዚህ እንደወደድኸኝ አወቅሁ፣

12. እኔን ግን ስለ ቅንነቴ ተቀበልኸኝ፣ በፊትህም ለዘላለም ታኖረኛለኽ።

13. ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ፣፡ የኢትዮጵያ (እሥራኤል) አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ አሜን። አሜን።

መዝሙር 120 (121)

1. ዓይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፣ ረዳቴ ከወዴት ይምጻ።

2. ረዳቴ ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፣።

3 እግሮችኽን ለመናወጥ አይሰጣቸውም፣ የሚጠብቅኽም አይተኛም።

4. እነሆ ኢትዮጵያን (እሥራኤልን)የሚጠብቅ፣ አይተኛም፣ አያንቀላፋምም።

5. እግዚአብሔር ይጠብቅኻል፣ እግዚአብሔር በቀኝ እጅኽ በኩል ይጋርድኻል።

6. ፀሐይ በቀን አይያቃጥልህም፣ ጨረቃም በሌሊት።

7. እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅኻል፣ ነፍስኽንም ይጠብቃታል።

8. ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ፣ እግዚአብሔር መውጣትኽንና መግባትኽን ይጠብቃል።

ክፍል

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ ?

የጸሎት ቦታችንን ቤተመቅደስ እናድርገው

5.1 የጸሎት ክፍልና ቤተመቅደስ ምን ያገናኛቸዋል?

ከሚቀድመው ፣ ከመካከልና ከሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አያይዘን ይህንን ርዕስ ማሳየት እንችላለን።

(ኦሪት ዘፍጥረት ምዕ. 4)

3፤ ከብዙ ቀን በኋላም ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረበ፤

4፤ አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኩራትና ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ

ቃየን ከምድር ፍሬ አቀረበ። የአቤል መስዋት ግን በኩራትና ከተመረጠ የተሰጠ መስዋት ነው።

እኛስ ታዲያ ዛሬ ላይ የትኛው ወንድም ነን? ቃየን? ወይስ አቤል ?

ቁምነገሩ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ሁሉ ፍቅር ያለበት ፣ ጥንቃቄ ያለበት ፣ አምላካዊ ክብሩን የሚገልጥ ፣ ኃይሉን የሚናገር ፣ ጸጋውን የሚጠይቅ መሆኑ ላይ ነው። አቤል በቃ ከሰቡት በጎች መካከል መርጦ በኩራት አቀረበ። አያችሁ። ሲሰጥም ኮርቶ ነው። አሁን አንዳንዶቻችን ተገደን እንደምንሰጥ አድርገን እናስባለን። የውለታ ጉዳይ ይመስለናል። እንደዚህ አይሰራም።

"በቃ ይኼ ለአምላኬ የተገባ መስዋቴ ነውና መድኃኔዓለም ሆይ ከእውነቴ ሰጠኹህ፥ አንተ በቸርነትህ ተቀበለኝ። ለሕይወቴም ሰማያዊ እምነትን ፣ ተስፋን ፣ ፍቅርና ክብርን ስጠኝ። "

ስንል ነው የሚሰራው። ተሰቆንቁነን የሰጠነው ሲመጣም ተሰቆንቁኖ ነው። ምን እንጠብቅ ታዲያ? ስጡ ይሰጣችኃል ነው እኮ።

✔ ቤተመቅደስም ሲሰራ ዝምብሎ በዘፈቀደ አይደለም። በራእይ ታይቶ ፣ በሰማያዊ መረጃና እውነት ተይዞ ፣ በተስፋውና በቃልኪዳኑ ኃይል ተቁሞ ፣ በጸጋው በረከትና በቅዱስ መንፈስ ሞገስ ተጎብኝቶ በጸሎትና በስግደት ጊዜያትን በማለፍ ነው ቤተመቅደስ የሚገነባው። የሚገነባበትም ቦታ ተመርጦ ነው። ልክ አቤል ከበጎቹ የሰቡትን እንደመረጠው። የሚሰጠውም መስዋት የንጹህ ፍቅር ተምሳሌ ነው። ቅዳሴው ፣ ቃሉ ፣ ዝማሬው ፣ ጸሎቱ ፣ ምሕላው ፣ ስግደቱ ሁሉ በፍቅሩ በኩል ሲያልፉ መድኃኔዓለም የአቤልን መስዋት እንደተመለከተ ሁሉ የቅድስት ቤተክርስቲያንን ቤተ መቅደስንም ይመለከታል።

✔ የጸሎት ቤትም ሲሰራ በዘፈቀደ ባይሆን መልካም ነው። ዝም ብሎ ስዕለ አድንኖዎቹን ለጠፍ ለጠፍ አድርጎ መቀመጥ አይደለም። እንደ ቤተ መቅደስ ሥርአት የጠበቀና በፍቅር መስዋት የተሰራ ቢሆን እግዚአብሔር ይመለከተዋል። ወደ አቤል መስዋት ተመልክቷላ። ስለዚህ ክፍሉን (የጸሎት ቦታውን ተጠንቀቁለት)። ቤተመቅደስ ስትገቡ የምታደርጉትን አድርጉበት። ቤተመቅደስ ስትገቡ ከማድረግ የምትቆጠቡትን ሁሉ ተከልከሉበት። እንዲህ የምታደርጉት እግዚአብሔር ከተመረጠውና ከተወደደው የፍቅር መስዋት መካከል ይገኛልና ነው።

< ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን፤ እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን። > መዝ. 131/132፥7

እግሮቹም በሚቆሙበት እንሰግዳለን አለ። የት ነው እንሰግዳለን የሚለው? እግርቹ በሚቆሙበት። አሁን እዚህ ጋር የእግዚአብሔር ፍቅርና ክብር የምንከተል ከሆነ አንድ ጥያቄ እንጠይቃለን። የእግዚአብሔር እግሮች የት ይቆማሉ??

አዎ! ይኼ ነው ጥያቄው። እግሮቹ በሚቆሙበት እንሰግዳለን ካልን እግሮቹ የት የት ይኖራሉ ነው ጥያቄው።

በመሠረቱ ልዑል እግዚአብሔር በአምላክነት ጥበቡ በሁሉ የመላ ነው። እዚህ ቦታ እግዚአብሔር አይኖርም ማለት አንችልም። ሁሉም በእርሱ ከእርሱም ነውና። ግን ቅዱስ ዳዊት ሊነግረን የፈለገው እግዚአብሔር በሚመሰገንበት ቤት

ሁሉ የፍቅሩ ኃይል በዚያ ይኖራልና የሚለውን ሊያሳስበን ነው።

✔ከምድራዊ ቤቶች ውስጥ አንደኛ የእግዚአብሔር ቅዱስ ማደሪያ ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት። ቤተመቅደሷም ውስጥ ጽላቷን በጥንቃቄ የምታስቀምጠው ይኽንን የእግዚአብሔር ማደሪያነቷን ጠንቅቃ ስለምታውቅ ነው።

✔ሁለተኛው ቤት ደሞ የጸሎት ክፍላችን መሆን አለበት። እግሮቹ በጸሎት ቤታችን ውስጥ እንዲቆሙ እግዚአብሔርን "ና ወደ ቤቴ ግባ ማለት አለብን።" ይኸው ላንተ የሰጠኹት ነውና እስኪ አባቴ እየው እንዴት ነው በሉ። ሊያየውም ዘንድ ሲመጣ እግሮቹን በዛው ቤታችን ያቆማል። አያችሁ ለዚህ ነው የጸሎት ቤት በፍቅርና በጥንቃቄ ስሩ የምለው። ስሙ የሚጠራበት ፣ የሚሰግደበት ፣ የሚጸለይበትና ጠላትን የምንቃወምበት ቅዱስ ስፍራችን ነውና እግዚአብሔር በዚያ ይኖራል። ግን በዚያ ሊኖር የሚችለው ለእርሱ የሚሆነውንና ለእርሱ የተገባውን ብቻ ስንሰጥ ነው። ቅዱስ እግዚአብሔር ከቅድስት ቤተመቅደስ ዘወትር እግሮቹ እንደቆሙ አለ። ምክንያቱም ቦታው በፍቅርና በክብር ተጠብቆ ይቆያልና። አባቶቻችን ለቤተመቅደስ የሚሳሱትን ያኽል ለሕይወታቸው ቅንጣት አይሳሱም። ስለዚህ የቤታችንንም ጸሎት ቤት በባለቤትነት ለእግዚአብሔር እንስጠው። ሳስተንም ዕለት ከዕለት እናምልክበት። ይኼ በፈረንጅ ቲዎሪና በዘመኑ አኗኗር ናላችሁ ለዞረ አይገባችኹም። ግን ለገባቸው ሁሉ እንደ ዳዊት ይናገራሉ። እንዲህ ይላሉ። "ወደ ማደሪያው እንገባለን ፥ እግሮቹም በሚቆሙበት ስፍራ ሁሉ እንሰግዳለን።"

< ኢየሱስም፣ “የቄሣርን ለቄሣር፣ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ” አላቸው። ማር. 12፥7 >

የሚደንቅ ቁልጭ ያለ ቃል ነው። በቃ የቄሣርን ለቄሣር እንስጠው። ለሰው የሚሰጠው ለሰው ነው። ለመንግሥት የሚሰጠው የመንግሥት ነው። ለኑሮ የሚሰጠው የኑሮ ነው። ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ደሞ የእግዚአብሔር ነው። የሚሰጠውን እንለይ። እንደ አቤል መርጠን እንስጥ። በእርግጥ ቤተክህነት ውስጥ ያሉት ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አይስጡ እንጂ ቤተመቅደስ'ስ ለእግዚአብሔር ከተሰጠች ዘመናትን አስቆጥራለች።

✔የኛም የጸሎት ቤት ለእግዚአብሔር መሰጠት አለበት። የቄሣርን ለቄሣር ፤ የኔን ደግሞ ለእኔ ስጡ አለ ጌታ። ለይታችሁ ስጡ አለ። ለሰው ከሰጠነው ሰው ነው የሚመልስልን። ለእግዚአብሔር ከሰጠነው ግን እግዚአብሔር ይመልስልናል። አስታውሱ ቃሉን "የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ" ነው የሚለው። ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ላይ ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ የተገባ አድርገን ነው መስጠት ያለብን። ለሥራ ቅጥር የምናስገባው ደብዳቤም ሆነ ማመልከቻ የመስሪያ ቤቱን የቢሮ ሕግ የጠበቀ ፣ ለመስሪያ ቤቱ የተስማማ ፣ መስሪያ ቤቱም የወደደው መሆን አለበት። የቄሣርን ለቄሣር ነዋ። ሰይጣንም እኮ የራሱን ይለያል። አሁን የዛር መናፍስት ጨሌ ፣ የተብረቀረቀ ቀሚስ ፣ ባለሦስት ጡት ጀበና ፣ ጨለማ ፣ የእንስሳት ደም ሌላም ሌላም የሚሰጠው ለራሱ የተስማማው ስለሆነ ነው። ታዲያስ የእግዚአብሔር እንዲሁ ይሰጣል እንዴ? በእግዚአብሔር የተመረጠ ፣ የተወደደ ፣ የተቀደሰ መስዋት ነው መስጠት ያለብን። የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር።

በቃ ሌላ ምንም ውስብስብ ቀመር የለውም። የጸሎት ቤታችንንም ለእግዚአብሔር በሚሆን ፍቅር ፣ ክብርና ጥንቃቄ እንያዘው። ይኽንን የምናደርገው ደሞ ለራሳችን ስንል ነው። እንጂ ከእግዚአብሔር ክብር የሚጨምረው አሊያ የሚቀንሰው አንዳች የለም። ለእግዚአብሔር የሚስማማውን ካልሰጠን ፤ እንደቃየን መስዋት አግበስብሰን ከሰጠን ወደኛ ፊቱን እንዲመልስ አንጠብቅ። ልዑል እግዚአብሔር የዞረው ወደ አቤል ነው። ወደ ቃየን አይደለም። እንኪያስ ለራሳችን ክብር ስንል የጸሎት ቤታችንን ለእግዚአብሔር እንስጥ። አለበዚያ ክብርህን የሚነጥቅህ ዓይነጥላው ፣ ዛሩ ፣ ቡዳው ፣ መተቱ ፣ አፍዝ አደንግዙ ወደ ሕይወትህ ይገባል። ጸጋህን ፣ ምገስህን ፣ ዕድልህንና በረከትህን ይሰልብሃል። ስለዚህ ለራስህ ስትል የጸሎት ቤትህን በጥንቃቄና በፍቅር ያዘው። ከልብህም ተንበርከክ። ከፍቅርህም ጸልይ። ከእውነተህም ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ስጥ። አብዝቶ ይሰጣሃልና

ክፍል ▬ ፭

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ ?

6.1 ስግደት

ክርስትና በአንደበት ብቻ አይኖርም። በመምሰል አይገፋም። ማህተብ በማሰር ብቻ አይገለጽም። ብዙ በማገልገል ብቻ አይጸናም። በጾም ጸሎት ብቻ አይገደብም። ቤተክርስቲያን በመሳለም ብቻ አይወሰንም። አድባራት በመጎብኘት ብቻ አይገደብም። የክርስትና መሠረት ይኽ ቅዱስ ቃለ-ትእዛዝ ነው።

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 22)

37፤ ኢየሱስም እንዲህ አለው። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ።

38፤ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።

ታላቂቱና የቀደመቺው ትእዛዝ ይኽቺ ናት። ፍጥረታት ሁሉ ከዚህች ትእዛዝ ይነሳሉ። የሰው ልጆች የመጀመሪያ ትልቂቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብሀ ፥ በፍጹም ነፍስህም ፥ በፍጹም አሳብህም ውደድ።

መውደድን ከምን አስነስቶ ጠቆመ? ከልብ። መውደድ ከልብ ይጀምራል። ዘወትር በሄድንበትና በቆምንበት ሁሉ፣ በሆነልንና በማይሆንልንም ልክ፣ ከውስጣችን አምላክን ማፍቀር ከልብ መውደድ ነው። ይኽ የልብ መውደድ ወደ ነፍስ ይኼዳል። 'እኔ' እንተውና 'እርሱ' እንላለን። 'ከእርሱም ለእርሱ' እንላለን። እስከ ጥልቅም መስዋትነት እናፈቅረዋለን። በመጨረሻው በፍጹም አሳብህ ይላል። አሳብ ታዲያ በሕሊናችን ጓዳ ተጸንሶ ወደ ውጪ የሚወለድ ግልጽ ውጤት እንጂ ተጨንግፎ የሚቀር ብቻ መሆን አይገባውም። መገለጥ ይገባዋል። መታየት ይገባዋል። መተግበር ይገባዋል።

እነሆም ከልባችን አስጀምረን፤ በነፍሳችን አኑረን በአሳባችን የምንይዘው ፍቅር የሚታየው በምግባራችን ብቻና ብቻ ነው። የሚጨበጠው ሲተገበር ነው። የሚኖረውም ሲተገበር ነው። እውነታነቱም የሚታየው በማድረግ ሲገለጥ ነው። ማውራትማ ሁሉ አንደበት ያለው ይችላል። "እወዳለሁ" ማለትማ ቀላል ነው። መናገርማ ያልወደደም እኮ ይችላል። ከልቡና ከነፍሱ የወደደ፤ ለይስሙላ ከወደደው እንኪያስ ከተግባር ውጪ በምን ይለያል ?

ስግደት አንዱ ታላቅ የፍቅራችን መግለጫ፣ የመገዛታችን መታያ፣ የአክብሮታችን ውጤት፣ የተፈጥሮአችን ዓላማ፣ የጸጋችን መነሻ፣ የሞገሳችን ምንጭ፣ የኃይላችን መገኛ፣ ዲያቢሎስን ማሸነፊያ፣ በጠቅላላው እንደ እስትንፋስ መኖሪያ ነው።

እናስተውል!!!

ዲያቢሎስና የሰው ልጆች የምንለይበት ትልቁ ድንበር ስግደት ነው። ክፉ ኃይላት ከሰማይ የተባረሩት አንገዛም ብለው ነው። አንሰግድም ብለው ነው። አንወድቅም ብለው ነው።

ታዲያም የሰው ልጅ በወደቀው የጨለማው ሠራዊት ምትክ ክብሩን ለመውረስና ምሥጋናውን ለማድረስ ሲፈጠር ይኽንን ተከትሎ ነው። አንወድቅም ባሉት ሠራዊት ፋንታ እንወድቃለን የሚሉን፣ አንገዛም ባሉት

ሠራዊት ፋንታ እንገዛለን የሚሉን፣ አንሰግድም ባሉት እብሪተኞች ምትክ የሚሰግዱ የሰው ልጆችን እግዚአብሔር አምላክ ፈጠረ።

እንኪያስ ስግደት ከክፉው መለያ ነው። የክርስትና ማንነት ነው። አምላክ አለኝ የምንልበት ነው።

❖ ፍጥረት ሁሉ ለአምላክ ይገዛል ❖

6.2 ስግደት ስንት አይነት ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ከአፈጻጸም ሥርዐት አንፃር ስግደት በሦስት ይከፈላል።

እነርሱም፡

- ❖ ሰጊድ/ ወዲቅ
- ❖ አስተብርኮና
- ❖ አድንኖ በመባል ይታወቃሉ።

✔የመጀመሪያው የስግደት አፈጻጸም ሥርዐት መሬት ላይ በመውደቅ ወይም ሙሉ በሙሉ ተደፍተው የሚሰግዱት ስግደት ሲሆን በልዩ ስሙ ወዲቅ በመባል ይታወቃል። ቃሉን ተመልከቱ።

"ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ።" (የዮሐንስ ራእይ 19፥10)

"ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሣ፤ ፊቱን_ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ፥" (ኦሪት ዘፍጥረት 19፥1)

"ሰገደም በግንባሩም ተደፋ" /ዘኁ.22፡31/ "በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደ" /ኢያ.5፡13/ "ማቅ ለብሰው በግንባራቸው ተደፉ" /1 ኛ ዜና.21፡16/ "በፊቱ ወደ ምድር ተደፉ" /2 ኛ ነገ. 2፡15/ "በእግሩ አጠገብ ወደቀች፤ በምድርም ላይ ተደፋች" /2 ኛ ነገ.4፡8/ "ከእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት" /ሐዋ.10፡25/ የሚሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ወዲቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው የስግደት ዐይነት መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው።

✔ሁለተኛው የስግደት ዐይነት አስተብርኮ በመባል ይታወቃል። ይህም ስያሜው እንደሚጠቁመው ጉልበትን ሸብረክ በማድረግ፣ በጉልበት በመቆም ወይም በመንበርከክ የሚፈጸም ነው።

"ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥" (ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 2፥10)

✔ሦስተኛው የስግደት አፈጻጸም ዐይነት አድንኖ ይባላል። አድንኖ ራሥን፣ ግንባርን፣ አንገትን ዝቅ በማድረግ የሚሰገድ ነው - "አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ..." እንዲባል በቅዳሴ። ይህም እንደቀደሙት ሁለቱ የስግደት አፈጻጸም ዐይነቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ነው። በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 49 ቁጥር 23 ላይ "ግንባራቸውን ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል" ይላል። ካህናትም "በንስሐ ውስጥ ያላችሁ ራሣችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ" ማለታቸው አድንኖን በመፈጸም ስገዱ ሲሉን ነው።

ወዲቅም፣ አስተብርኮም ሆነ አድንኖ የስግደት አፈጻጸም ዐይነቶች ናቸው እንጂ ከስግደቱ ዓላማ ጋር ወይም ከሚሰገድለት አካል አንጻር የሚፈጸሙ አይደለም። በሌላ አገላለፅ ሦስቱን የስግደት ዐይነቶች ስግደት ለሚገባው ሁሉ እንፈጽማለን - ሦስቱንም ዐይነት ስግደት ለእግዚአብሔርም ለቅዱሳንም እናቀርባለን።

6.3 ስግደት በስንት ይከፈላል?

ቅድስት የተወደደች ርትዕት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አስገንዝባ እንደምታስተምረን ስግደት በመሠረቱ በሁለት ይከፈላል። እነርሱም፡

- ❖ የአምላክ ስግደት እና
- ❖ የጸጋ አማልክት/ የቅዱሳን ስግደት በመባል ይታወቃሉ።

እነዚህ ሁለቱ ደግሞ በውስጣቸው ለሁለት ይከፈላሉ። እነዚህም

- ❖ የአምላክ ስግደት - በውስጡ የአምልኮንና የንስሐ ስግደትን ይይዛል
- ❖ የቅዱሳን ስግደት - በውስጡ የጸጋንና የክብርን ስግደት ይይዛል።

ስለዚህ ስግደታት በጠቅላላው፡

- ✓ የአምልኮ ስግደት
- ✓ የንስሐ ስግደት
- ✓ የጸጋ ስግደት እና
- ✓ የክብር ስግደት በመባል ይከፈላሉ።

4 ቱንም ስግደታት በተናጠል ለምን እንደሚሰገዱ፣ ምን እየተባሉ እንደሚሰገዱ፣ መቼ መቼ እንደሚሰገዱ በዝርዝር እንዳስሳለን።

ክፍል ፪

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ?

ስግደት

7.1 የአምላክ ስግደት

ከ 4 ቱ ስግደታት የመጀመሪያውና ኃያሉ ስግደት ይኽ ስግደት ነው። የአምላክ ስግደት። የአምልኮ ስግድት። ይኽ ስግደት የሚሰገደው በልዩ ሦስትነት በተዋህዶ አንድነቱ ለምናመልከው ለእግዚአብሔር ብቻና ብቻ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን አስቀድሞ ስለኖረ ሕላዌነቱ፣ ዓለምንም ስለመፍጠሩ፣ ዓለምንም አሳልፎ ስለመኖሩ፣ ከሁሉ በላይ ያለ አንድ አምላክ ስለመሆኑ፣ ሁሉ ከእርሱ በእርሱ ለእርሱ ሰለመሆኑ፣ ስለ ባሕሪ ፈጣሪነቱ ፍጥረት ሁሉ ይገዛ ዘንድ ይገባዋል። የቀደመውን የሕግ ትዕዛዝ እናስተውል!

"አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።" (የማርቆስ ወንጌል 12፥30)

ይኼ ቃል የምንም ነገር መነሻው ነው። ስለዚህም ነው ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት ያለው።

በጣም በሚገርም ሁኔታ የዘመናችን ክርስቲያን ይኽንን የአምላክ ስግደት እስከመኖሩም የረሳ ብዙ በጣም ብዙ ሰው አለ። የአምልኮ ስግደት ምን እንደሆነ የማያውቁ ሰንበት ተማሪያን፣ ዘማሪያን፣ ዲያቆናት፣ ቀሳውስትና አባቶች ጭምር በዘመናችን አሉ። ቃሉ ግን እንደዚህ ይላል።

"እኔ ሕያው ነኝ፥ ይላል ጌታ፥ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል መላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ተብሎ ተጽፎአልና።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 14፥11)

ጉልበት ሁሉ ነው ያለው። ጉልበት ሁሉ ለእግዚአብሔር ይንበረከካል። የአምልኮት ይሰገዳል። ለፍቅሩ ይወድቃል። ይኸው ነው።

የአምልኮት ስግደት ለአጋእዝተ ዓለም ሥላሴ ብቻ ነው የሚሰገደው። ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ እየተባለ ነው የሚሰገደው። ከአምላክ ውጫ ይኽ ስግደት አይሰገድም!

"ያን ጊዜ ኢየሱስ። ሂድ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው።" (የማቴዎስ ወንጌል 4፥10)

ጌታችን ራሱም በሰማያዊ ቃሉ 'ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ' ብሎ የአምልኮት ስግደት የሚገባው ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ጠቁሞናል።

ይኽን ስግደት የማይሰግድ ክርሰቲያን በቀጥታ ቋንቋ አምላክ የለኝም እያለ ነው በምግባሩ። እርሱን አምልክ ስግደትም ስገድ ብሎ ቃሉ ከተናገረ፤ ከዚህ ውጪ አልሰግድም ካልክ እንግዲያውስ ያለምንም ጥያቄና መልሰ አልሰግድም ብሎ ወደ ምድር የተጣለው የጨለማ ሠራዊት ጋር ህብረት በውድም በግድም ፈጥረሃል ማለት ነው። ይሕንን ሕዘበ ክርስቲያን በአጽንኦት ሊገነዘብ የግድ ነው። በቃ አማራጭ የለም። ሦስተኛ መንገድ የለም። እሳት ወይ ወኃ። ብርሃን ወይ ጨለማ። ግራ ወይ ቀኝ። ገልለተኛ ዓለም የለም። መኃል የሚባል ነገር የለም። በውድ ካልሰገድክ በግድ የሚያደቅህ ባለጋራ አለ። ያለ አምልኮ ደግሞ በምንም በየትም በማንም አታሸንፈውም። ይሕንኑ መመሪያ ጌታችን እንዲሁ ሰጥቶናል።

< ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ። >

ሰይጣንን ሂድ ሲለው ጌታችን ዝም ብሎ አይደለም። ማሸነፊያውን ቃል እንዲህ ሲል አስቀምጦት ነው። ለጌታ ለአምላክህ ስገድ።

7.2 የአምልኮ ስግደት መቼ መቼ ይሰገዳል?

የአምላክ ስግደት አይቋረጥም!!! በፍጹም አይቋረጥም!!! ዘወትር ከእሁድ እስከ እሁድ ከዓመት እስከ ዓመት አይቆምም።

አምላክን ማምለክ በቀን አይወሰንም። አምልኮ በጊዜ አይገደብም። ቢሆንልን እያንዳንዷን ሰኮንድ በምስጋና በቆምን።

የዘመናችን ክርስቲያኖች የአምልኮን ስግደት በሰንበት፣ በግዝት በዓላትና በበዓለ 50 ቀናት አትስገዱ ሲሉ ይሰማሉ።

አስተውሉ!!!

የአምልኮ ስግደት በምንም ቀናት በምንም መልኩ አይቋረጥም!!!

ሦስቱ ስግደታት የራሳቸው ጊዜያትና ቀናት አሏቸው። የአምልኮ ስግደት ግን ልብ በሉ ዘወትር አይቆረጥም! አንድ ክርስቲያን ቢያንስ በቀን ሁለቴ የአምልኮ ስግደትን ከሕይወቱ ማራቅ የለበትም።

7.3 የአምልኮ ስግደት እንዴት ይሰገዳል?

ከሦስቱ የስግደት አይነቶች ከሆነው ሰጊድ አሊያም ወዲቅ የምንለውን ስግደት እንሰግዳለን።

ምክንያቱም፡

1ኛ. ሙሉ በመሉ ወድቀን የአምልኮታችንን ፍቅር ለሥላሴ እንገልጥበታለን

2ኛ. ስግደት አንዱ የዲያቢሎስ መውጊያ ኃያል መሳሪያ ነውና እየተቃወመ ያስቸገረን ጠላት 'በቃለ-ኪዳን' ጸሎት በማሳሰብ ግንባር ላይ አስረነው በምንሰግድበት ጊዜ ምንጣፋችን ላይ የቅዱስ ሚካኤልን ምስል ልክ ሰይፉ ላይ ወይንም ደርቅ የእንጨት መስቀል ላይ አሊያ የጸለይንበት ቅዱስ መጽሐፍ ላይ ግንባራችንን እያስነካ ስንሰግድ የክፉውን ኃይል እንሰብርበታልና።

7.4 ምን ምን እያልን እንሰገድ?

የአምልኮት ስገደት የአምላክ ስግደት ነው። ስለዚህም ለአምላክ የተገባ የሆነ ስግደትን ብቻ እንሰግዳለን። ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ እያልን እንሰግዳለን።

ጀማሪ ከሆናችሁ 21 21 ጠዋትና ማታ መስገድ። ከበረታችሁም እየጨመራችሁ ስገዱ። ከታች የምትመለከቱት ስግደት 41 ጊዜ ለመስገድ የተሰናዳ ነው። የጸሎት ቦታችሁ ውስጥ በወረቀት አስወጡትና እስክትሸመድዱ ፊት ለፊት አድርጋችሁ እያያችሁ ስገዱ።

1) የአምልኮ ስግደት

- ✓ ለአጋእዝተ ዓለም ሥላሴ የሚሰገድ
- ✓ አምልኮን የሚገልጽ
- ✓ መቼውንም የማይቋረጥ ስግደት ነው።

የአምልኮ ስግደት

(ማስታወሻ 3X ማለት 3 ጊዜ በሉት እንደማለት ነው። ለምሳሌ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ 1..ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ 2..ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ 3)

እሰግድ ለአብ

እሰግድ ለወልድ

እሰግድ ለመንፈስ ቅዱስ

ስብሐት ለአብ

ስብሐት ለወልድ

ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ

ምስጋና ለኩሉ አብ

ምስጋና ለኩሉ ወልድ

ምስጋና ለኩሉ መንፈስ ቅዱስ

ሃሌሉያ ለአብ

ሃሌሉያ ለወልድ

ሃሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ (3X)

ቅዱሰ እግዚአብሔር ፣

ቅዱስ ኃያል ፣

ቅዱስ ሕያው

ቅዱስ ጸባኦት ፣

ቅዱስ አዶናይ ፣

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ ያህዌ

ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል

ቅዱስ ኢያኤል

ቅዱስ ታዳኤል

ቅዱስ ማስያስ

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ(3X)

ይህንን ኀብስት ላበላን ..ምስጋና ይገባል

ይህንንም ጽዋ ላጠጣን ..ምስጋና ይገባል

ምግባችንንና ልብሳችንንም ላዘጋጀልን ..ምስጋና ይገባል

ኃጥኢታችንንም ሁሉ ለታገሠልን ..ምስጋና ይገባል

ክቡር ደሙን ቅዱስ ሥጋውን ለሠጠን ..ምስጋና ይገባል

እስከዚችም ሰዓት ላደረሰን ..ምስጋና ይገባል

በጸጋው ለጠበቀን ..ምስጋና ይገባል

ቸርነቱን ላበዛልን ...ምስጋና ይገባል

ፍጹም ፍቅሩን ለሠጠን ..ምስጋና ይገባል

ለድንግል ማርያም ልጅ ..ምስጋና ይገባል

ኦ ቅድስት ሥላሴ አምልኮም ምስጋናም ክብርም ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ይሁን አሜን።

ይኼ ለበረታችሁና ክፉ መናፍስትን ለማድከም የሚሆን ኃያል ስግደት ነው። ክርስትና የተሸፋፈነ አንዳች የለውምና ሰግዳችሁ ተጠቅማችሁ ያለውን ኃያልነት በሕይወታችሁ እዩ።

የአምልኮ ስግደት

ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ወደኔ ና:: x3

አማኑኤል ሆይ ወደኔ ና:: x3

መድኅኒትዓለም ሆይ ወደኔ ና:: x3

ለአብ፣ እሰግዳለሁ:: x 3

ለወልድ፣ እሰግዳለሁ:: x 3

ለመንፈስ ቅዱስ እሰግዳለሁ:: x 3

አብ ቅዱስ ነው:: x 3

ወልድ ቅዱስ ነው:: x 3

መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው:: x 3

አብ ፅሐይ ነው:: x 3

ወልድ ፅሑይ ነው:: x 3

መንፈስ ቅዱስ ፅሑይ ነው:: x 3

አብ ፍቅር ነው:: x 3

ወልድ ፍቅር ነው:: x 3

መንፈስ ቅዱስ ፍቅር ነው:: x 3

አብ እሳት ነው:: x 3

ወልድ እሳት ነው:: x 3

መንፈስ ቅዱስ እሳት ነው:: x 3

አብ ብርሃን ነው:: x 3

ወልድ ብርሃን ነው:: x 3

መንፈስ ቅዱስ ብርሃን ነው:: x 3

አብ ጉንድ ወይን ነው:: x 3

ወልድ ጉንድ ወይን ነው:: x 3

መንፈስ ቅዱስ ጉንድ ወይን ነው:: x 3

አብ መለኮታዊ ቀስት ነው :: x 3

ወልድ መለኮታዊ ቀስት ነው :: x 3

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ቀስት ነው :: x 3

አብ መለኮታዊ ብርሃን ነው:: x 3

ወልድ መለኮታዊ ብርሃን ነው:: x 3

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ብርሃን ነው:: x 3

አብ የሃይማኖት መስረት ነው:: x 3

ወልድ የሃይማኖት መስረት ነው:: x 3

መንፈስ ቅዱስ የሃይማኖት መስረት ነው:: x 3

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይልካል:: x 3

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያስለጥናል:: x 3

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ምስክር ይሆናል:: x 3

አንዱ አብ ቅዱስ ነው:: x 3

አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው:: x 3

አንዱ መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው:: x 3

ምስጋና ይሁን ለአብ:: x 3

ምስጋና ይሁን ለወልድ:: x 3

ምስጋና ይሁን ለመንፈስ ቅዱስ:: x 3

በረከቱን ለሰጠን፣

ሀይሉን ላበዛልን፣

በዚህ ሰአት ላቆመን፣

በቸርነቱ መንገድ ለመራን፣

በዚህ ሰእት በጸጋ ለጠበቀን፣

በብርሀኑ ሐይል ለመራኸን፣

ላንተ ክብር ምስጋና ይግባው፣

ሐሌሉያ ለአብ:: x 3

ሐሌሉያ ለወልድ:: x 3

ሐሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ:: x 3

ቅዱስ እግዚአብሔር፣

ቅዱስ ሐያል፣

ቅዱስ ሕያው፣

ቅዱስ ኤልሻዳይ፣

ቅዱስ አዶናይ፣

ቅዱስ ያህዌ፣

ቅዱስ ጸባኦት፣

ቅዱስ ኢየሱስ፣

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል፣

የድንግል ማርያም ልጅ፣

ክብር ምስጋና ይግባው::

ክፍል - ፰

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ?

ስግደት

8.1 የንስሐ ስግደት

ንስሐ ፦ ነስሐ ተፀፀተ ካለው የተገኘ ሲሆን ፤ ንስሐ ማለት በሠሩት ኃጢአት መፀፀት ፣ ማዘን ፣ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ መወሰን ማለት ነው። ንስሐ ከዘለዓለማዊ ፍርድ የሚያድን ፤ ዘማዊውን እንደ ድንግል ፤ ሌባውን መጽዋች የሚያደርግ በፊት ከተሠራው ኃጢአት ንጹህ አድርጎ ፤ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርግ ምሥጢር ነው ።

ብዙዎች የዘመናችን ክርስቲያኖች ታዲያ የሚያውቁት ስግደት የንስሐን ስግደት ነው። በሰሞነ ህማማትና በዕለተ ስቅለቱ ቅድስት ቤተክርስቲያን በመገኘት በዓመት 6 ቀን ላልበለጠ ጊዜ ብቻ መስገድን እናውቃለን። የአምልኮት ስግደት፣ የጸጋና የቅዱሳን ስግደት በክርስቲያኑ ልብና ሕሊና ውስጥ ደብዛቸው ከጠፋ ዘመናት አልፈዋል። አሁን አሁንማ፤ በዓመት አንዴም ከምንሰግዳት ስግደት እየቆረጥን እየቆረጥን ስግደት የሚባለው ኃያል የእግዚአብሔር ጦር ዕቃን አርቀን ከወረወርን ቆየን። በዚህ ምክንያት ወደ ልባችንና ወደ ቤታችን ጤናችንን፣ ሰላማችንን፣ ደስታችንን፣ ጸጋችንን፣ ዕድላችንን፣ ተስፋችንን፣ ገንዘብና እውቀታችንን የሚወረውርብን ጠላት መጣብን።

የንስሐ ስግደት የሚሰገደው ለጌታችን ለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ቃሉን ተመልከቱ።

(ወደ ዕብራውያን ምዕ. 2)

16፤ የአብርሃምን ዘር ይዞአልና እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም።

17፤ ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ፥ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፥ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው።

ቃለ እግዚአብሔር በኃለኛው ዘመን በቃልነት ሕላዌው ሳለ ለአብርሃም በሰጠው ቃል ኪዳን መሠረት ከትውልዱ ዘር ተገኝቶ፤ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሥጋ ሆነ። ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በኛ አደረ። ይሕንንም የጌታችንን የምሕረት ጉዞ ሲጠቅስ የመልአክትን ያይደለ የአብርሃም ዘር ያዘ እንጂ አለ። እነሆም ጌታችን የሕዝብን ኃጥኢት ለማስተስረይ የታመነ ሊቀ ካህን ሆነ። መድኃኒዓለም በክህነት የካህናትም ሊቅ

ነውና የበደልን ስርየት ይቀበላል። ኃጥኢትንም ያጥባል። ንስሐንም ይሰጣል። እነሆም አስተውሉ ትልቁን ንስሐ የምንገባው መጀመሪያ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የምድር ካህናትም የጌታችንን ፈለግ ተከትለው ንስሐችንን ይቀበላሉ። ለካህን ብቻ ተናዘን፤ በጌታችን ፊት ለንስሐ መውደቅ ካቃተን እንግዲያውስ በድጋሚ ልባችንን ልንፈትሸና ልንመረምር ያስፈልገናል።

8.2 የንስሐ ስግደት መቼ መቼ ይሰገዳል?

ይሕንን ጥያቄ መመለስ ያለበት ንስሐውን የሚያደረገው ክርስቲያን ነው። እንደ በደላችንና እንደ ንስሐችን ሁሉ ልንሰግድ ይገባናል። ቢሆንልን ዘወትርም ከአምልኮ ስግደት በተጨማሪ ብንሰግድ መልካም በሆነ ነበረ።

- የንስሐ ስግደት በሰንበትና በግዝት በዓላት አይሰገድም!!

ልብ በሉ!

የአምልኮ ስግደት አይቋረጥም!!

በበዓላትና በሰንበት የማንሰግደው የንስሐ ስግድትን ነው። ይሕን ከልባችሁ ሰሌዳ አድማቃችሁ ጻፉ!

- የንስሐ ስግደት በአጽዋማትና በሱባዔ ወቅት፤ እንዲሁም ንስሐ በገባን ጊዜ ይሰገዳል።

አሁንም ልብ በሉ***!***

የአምልኮት ስግደት አይቋረጥም። ሱባዔ ብንይዝ፣ ጾሞ ላይ ብንሆን፣ ንስሐ በገባንም ጊዜ ሁለቱንም ስግደታት እንሰግዳለን እንጂ አንዱ በአንዱ አይተኩም!!

8.3 ምን ምን እያልን የንስሐ እንስገድ?

❶• የንስሐ ስግደት ለሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ይሰገዳል።

" እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።" (ወደ ዕብራውያን 4፥14)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊተኛው የሃይማኖት ሐዋሪያ፤ ኃይለኛው ሊቀ ካህናት ነውና የክህነት ማህረግ አለው። የካህናት ሁሉ ሊቅ ነው። እነሆም ንስሐ'ን ይቀበላል። የንስሐ ስግደት በሁለቱ ሰንበታት፤ በግዝት በዓላትና በበዓለ 50 ወቅቶች ላይ አይሰገድም።

ከታች የተዘጋጀው 41 41 ስግደት ነው። እንደ አብነት እንጂ ከዚህም በላይ መስገድና በንስሐ መንጻት ያስፈልገናል።

2) የንስሐ ስግደት

✔ ለሊቀ ካህናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምንሰግደው

✔ በደልን የምናዘዝበትና

✔ ማረን የምንልበት ስግደት ነው።

✔ በተለይ በጾም ጸሎት ጊዜያት በብርታት ከእንባ ጋር ይሰገዳል

የንስሐ ስግደት

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ 3X

እግዚኦ መሐረነ አማኑኤል 3X

እግዚኦ መሐረነ ጌታ ሆይ 3X

ኪርያላይሶን ጸባኦት

ኪርያላሶን አዶናይ

ኪርያላይሶን ያሕዌ

ኪርያላይሶን ኤልሻዳይ

ኪርያላይሶን ኢየሱስ ክርስቶስ

ኪርያላይሶን አማኑኤል

በእንተ እግዝእትነ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ 3X

በእንተ እግዝእትነ ማርያም መሐረነ አማኑኤል 3X

በእንተ እግዝእትነ ማርያም መሐረነ ጌታ ሆይ 3X

በእንተ ኪሩቤል መሐረነ ክርስቶስ

በእንተ ሱራፌል መሐረነ ክርስቶስ

በእንተ ካህናተ ሰማይ መሐረነ ክርስቶስ

በእንተ ነብያት መሐረነ ክርስቶስ

ይቅርታን ስጠኝ ቅዱስ ሆይ

ይቅርታን ስጠኝ አምላክ ሆይ

ይቅርታን ስጠኝ አባት ሆይ

ስለ ድንግል ማርያም ብለክ ይቅር በለኝ

ስለ ቅዱስ ሚካኤል ብለክ ይቅር በለኝ

ስለ ቅዱስ ገብርኤል ብለክ ይቅር በለኝ

ወንጌልህን ስለበሰበኩ ሐዋሪያትህ ብለክ ተለመነኝ

መከራን ስለታገሱ ሰማዕታትህ ብለክ ተለመነኝ

በክብርህም ስለከበሩ ጻድቃን ብለክ ተለመነኝ

ኦ አምላክ

ኦ ክርስቶስ

ያድኅነነ ከመአቱ ይሰውረነ በምሕረቱ

በእንተ ማርያም ወላዲቱ

ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ

ብለን 41 እንሰግድና እዛው እንደተንበረከክን

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ 12 ጊዜ ፤ በእንተ እግዝእትነ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ 12 ጊዜ በጣቶቻችን እንቆጥራለን።

ክፍል - ፱

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ ?

9.1 የቅዱሳን ስግደት

የቅዱሳን ስግደት እግዚአብሔር አምላክ ለወደዳቸው፣ ለመረጣቸውና ላከበራቸው ሁሉ የምንሰግደው ከመንፈስ ቅዱስ ጸጋቸው የምንካፈልበት፣ የእምነት ኃይላቸውን የምናገኝበት፣ የእምነት ታሪካቸውን እንደምሪት የምንይዝበትና እግዚአብሔር ያከበራችሁ እኛም እናከብራችኀለን የምንልበት ስግደት ነው።

" እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው?" (ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥33)

የቅዱሳን ስግደት ወደ ሁለት ይከፈላል።

እነርሱም፡

1. የጸጋና
2. የክብር በመባል ይታወቃሉ።

9.2 የጸጋ ስግደት

ይሕ ስግደት ለተወደደች ለተመረጠች ለከበረች የጸጋ ሁሉ ባለቤት ለሆነች ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ የሚሰገድ ስግደት ነው።

(የሉቃስ ወንጌል ምዕ.1)

48፤ እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤

49፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን 'ብፅዕት' የምንለው በአንደበት ብቻ አይደለም። እርሱንማ ያልተቀበላትስ ይለው የለም ወይ? በተግባር እንሰገዳለን። ለጸጋዋ እንሰግዳለን። የሰው ልጆች ሁሉ ስለሚመኩበት እናትነቷ እንበረከካለን። በማንም ያልሆነና የማይሆን የሀሳብም የሥጋም ንጽህነቷን እንመረኮዝበት ኃይል እንሰግዳለን። ከፈጣሪ በታች ከፍጡራንም በላይ እያሉ በአፍ ብቻ አውርቶ መቀመጥ መወደድን አይገልጽም። ይልቁኑ እንደከበረች ቅድሰት ኤልሳቤት 'የጌታዬ እናት እመብርሃን ሆይ፥ እንግዲያውስ የሰላምታሽን ድምጽ በሰማሁ ጊዜ እነሆ ጨናዬ፣ ሰላሜ፣ በረከቴ፣ ሞገሴ፣ እውቀቴ፣ ቤቴና ቤተሰቤም ሁሉ በደስታ ዘለለ' ስንል በስግደት እናመሰግናታለን።

እምዬ ድንግል ማርያም ፈጣን እናት ነች። እንኳንስ እየሰገዳችሁ በእንባ ተማጽናችሁ እንዲሁ ሰውን ለመርዳት የምትፋጠን እናት ነች። በያኔም ዘመን ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ነበረ የወጣቺው። ዛሬም ድረስ ለሰው ልጆች ምሕረት መፍጠን ያለች ክርስቶስ መድኃኒዓለምም በፍቅር ያያት የከበረች እናቱ እናታችን ናት። እኛና እግዚአብሔር በአማኑኤል አንድነታችን አንድ ጋር ሆነን እናታችን የምንላት የደስታ ባለቤት ነች።

9.3 የጸጋ ስግደት መቼ መቼ እንሰገድ?

ይሕን ለወላዲተ አምላክ ባላችሁ ፍቅር ልክ እናንተ መልሱት።

እንደ ንስሐው ስግደት አጠቃላይ የቅዱሳን ስግደት በሰንበትና ግዝት በዓላት አይሰገድም!

ከዚያ ውጪ ለቅዱሳኑ እንደፍቅራችሁ ልክ ስገዱ። እንደመውደዳችሁ መጠን ስገዱ። ምክንያቱም ከፍቅር ያስጀመርነው ስግደት ኃይሉ በመውደዳችን ልክ ነውና።

9.4 ምን ምን እያልን የጸጋን ስግደት እንሰገድ?

የጸጋ ስግደት

✔ ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ ይሰገዳል

✔ እመቤታችንን ከልቡ ያፈቀረና በተግባርም የሚያከብራት ዘወትር ይሰግዳል። በዕለተ ቀኖቿ ግን የማይቀር ስግደት ነው።

ከታች እንደምሳሌ 21 ስግደት ተቀምጧል። ከዚህ በላይ መጨመርና እየበረቱ መሄድ እመቤታችንን ከሚወድድ ሁሉ ይጠበቃል።

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የጸጋ ስግደት

ጸጋን የሞላብሽ ሆይ ..ደስ ይበልሽ

ጌታ ካንቺ ጋር ነውና ..ደስ ይበልሽ

ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽና ..ደስ ይበልሽ

የማኅጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነውና ..ደስታ ይገባሻል

የመድሃኒታችን እናቱ ላንቺ ..ደስታ ይገባሻል

በሰላምታሽ ደምጽ ተደስተናልና ..ደስታ ይገባሻል

ንግሥት ..የንጉሥ እናት

እመቤት ..የእግዚአብሔር እናት

ክብርት ..የአምላክ እናት

መቅረዝ ..የብርሃን እናት

ንጽሕት ጥጃ ..የነጭ በሬ እናት

ልዕልት ..በአርያም የሚኖር የልዑል እናት

ውድስት ..የምስጉን እናት

ምዕዝት ..የሸቱ እናት

የወርቅ ሣፅን ..የዕንቁ ባሕርይ መገኛ

በዕውነት ምስጋና ይገባሻል ..የእግዚአብሔር እናቱ ሆነሻልና

በዕውነት መደነቅ ይገባሻል ..ዓለምን በመሐል እጁ የያዘውን ወልደሻልና

በዕውነት ብፅዕነት ይገባሻል ..ለእውነተኛ ፀሐይ መውጫ ነሽና

በዕውነት መመስገን ይገባሻል ..ለማለዳው ኮከብ ምስራቅ ሆነሻልና

በዕውነት መደነቅ ይገባሻል ..ለጥምቀት ልጆች መመኪያ ሆነሻልና

በዕውነት ብፅዕና ይገባሻል ..ለሃይማኖት መሠረት ፅናት ሆነሻልና

ክፍል - I

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ?

10.1 የቅዱሳን ስግደት

ሁለተኛው የቅዱሳን ስግደት ከጸጋ ስግደት በመቀጠል የሚገኘው የቅዱሳን ስግደት ነው። የክብር ስግደት በመባል ይታወቃል።

የክብር ስግደት እግዚአብሔር መርጦ ላከበራቸው ሁሉ ቅዱሳን የተገባ ስግደት ነው።

" ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፥"(መዝሙረ ዳዊት 89፥3)

እንዲል ልዑል እግዚአብሔር በመረጠው ሁሉ ላይ ኃይለ ቃልኪዳኑ በዚያ ይኖራል። ስለዚህ ለተከበሩት ቅዱሳን መልአክት፣ ጻድቃን ሰማእታት፣ ሐዋሪያት፣ ነብያት፣ ቅዱስ መስቀሉ፣ ቅዱስ ታቦትና ለሁሉ የእግዚአብሔር ቅዱስ በክብር እንሰግዳለን።

10.2 መቼ መቼ የክብር ስግደት እንሰግዳለን?

በምሳሌ የቅዱስ ሚካኤልን ስግደት እንመልከት። እነሆም መቼ መቼ እንሰገድ የሚለውንም እነሆ ለቅዱስ ሚካኤል ባለን ፍቅር ይመረኮዛል። ዕለት ዕለትም መስገዳችን ታላቅ ነው።

እንደ ንስሐና ጸጋ ስግደታት ሁሉ በሰንበት ወቅት የክብር ስግደት አይሰገድም። ከዚያ ውጪ ግን የቀን ገደብ የለውምና በፍቅራችሁ ልክ ለቅዱሳኑ ስገዱ።

10.3 ምን ምን እያልን እንሰገድ?

ከታች የተቀመጠው 12 ጊዜ የተቆጠረ የቅዱስ ሚካኤል ስግደት ነው። ለሌሎችም ቅዱሳን በተመሳሳይ መልኩ እንደሚሰገድ ምሳሌ ለማስቀመጥ የተዘጋጀ ነው። የስግደት መጠናችንም ይሕን ያህል ብሎ የሚወስነው የልባችን ፍቅር እንጂ ሕግ አይደለም!

የክብር ስግደት ለቅዱስ ሚካኤል

እሰግድ ለቅዱስ ሚካኤል 3X

ኦ ሚካኤል 3X

የድኅንነት መልእክተኛ ሚካኤል ሆይ ሰላም እልሃለሁ

ድኃውን የምትንከባከበው ሚካኤል ሆይ ሰላም እልሃለሁ

ችግረኛውን ለመርዳት የምትላክ መልአክ ሆይ ሰላም እልሃለሁ

ከልዑል ስም አጠራር ጋር ለተባበረ ስምህ እሰግዳለሁ

ለነበልባላዊ ስእርተ ርእስህ እሰግዳለሁ

ከነፋስና እሳት ለተፈጠረ መልአካዊ ገጽታህ እሰግዳለሁ

የሌሎችንም ቅዱሳን ስግደት በተመሳሳይ መልኩ መስገድ ነው። ለመስገድ የምንጠቀማቸውን ቃላት ከመልክአቸውና ከጸሎት መጽሐፋት መውሰድ መንፈሳዊ ብልጠት ነው።

ክፍል - ፲፩

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ?

11.1 መቁጠሪያ



♦በጥንታዊቷ ቤተክርስቲያናችን ከሚገኙና ሰይጣን ዲያብሎስን ከምንዋጋበት መሣሪያዎቻችን መካከል አንዱ መቁጠሪያ ነው : :

"በአንተ ጠላቶቻችን እንወጋቸዋለን በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን " መዝ.43 (44)፥5

መቁጠሪያ ለሰው ልጅ በጣም ከሚያስፈልጉት በጸሎት ጊዜያት ውስጥ አንዱ ነው። ምክንያቱም ከዛሬ መቶ ሃያ አመት በፊት የነበሩ አባቶች በመቁጠሪያ ጸሎት በመጸለይ ኃይለ አጋንንትን በመቀጥቀጥ ድል ያድርጉ፤ ሥጋቸውንም ለነብሳቸው ያስገዙት ነበር። አሁን ግን ተረስቶ መቁጠሪያ ለቆራቢ ነው፤ መቁጠሪያ ለምንኩስና የበቁ ሰዎች ነው እየተባለ ይገኛል። ይኽ ስህተት ነው ።

በመጽሐፍ ቅዱስ 1 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 9፥27 ላይ ያለውን ቃል እንመልከት።

"ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ። "

እየጎሰምሁ ሲል እየቀጠቀጥኩ ማለቱ ግልጽ ነው።

11.2 መቁጠሪያን እንዴት እንጠቀምበት?

መቁጠሪያ በአጠረ አገላለፅ መንፈሳዊ ላብራቶሪ ነው። ውስጠኛ ክፍልህን ትፈትሽበታለህ። ይህንን የመቁጠሪያን አገልገሎት ቀደምት በተለይም ከ 60'ዎቹ ዘመን አስቀድመው የነበሩት አባቶቻችን በተገባ ያውቁታል። ከእነርሱም የእምነትና የታሪክ እውነት ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ ነው።

መቁጠርያ በመሰረቱ ቃሉ መ-ቁ-ጠ-ር-ያ ነው ራሱ ቃሉ። አባቶቻችን ማንበብ ስለማይችሉ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስን 41 ግዜ፣ ይቆጥራሉ፣ በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስን 41 ግዜ፣ ኪርላይሶን ክርስቶስን 41 ገዜ፣ አምላኬ አምላኬን 41 ግዜ፣ ስምዓነ አምላክነ 41 ግዜ፣ አድኅነነ ከመዓቱ ይሰውረነ በምሕረቱ በእንተ ማርያም ወላዲቱ 41 ግዜ ይሉ ነበር።

አብዛኛውን የት የት ይቀመጣል መንፈስ የሚለዉን ስናስተዉል

- ✔ ቀኝና ግራ ላይ ትከሻ፣
- ✔ ማጅራት አከባቢ ከኋላ፣
- ✔ አእምሮ እና ግንባር ላይ
- ✔ በተጨማሪ ዓይን ላይና እንደዚሁም ክንድ ላይ፣ እጅ ላይ፣ እግር ላይ። ወደ ሌላ መንገድ ሊወስድህና ሊመራህ ሲፈልግ እግር ላይ ነው የሚቀመጠው።
- ✔ በአኗኗር ባህሪ ደግሞ ልብ፣ ሕሊና፣ አእምሮ ላይ ነው የሚቀመጠው።
- ✔ የሚጸልይ ከሆነ ከዚህ ውጪ ባለ ክፍል ላይ ነው የሚቀመጠው። ጸሎት ከሌለ ግን ሕሊና፣ አእምሮ፣ ልቦና ላይ ነው የሚቀመጠው።

በዚህ ግዜ ሕሊና ከነፍሳችን አንደኛው ክፍል ነው። ልቦናም ከነፍሳችን አንደኛው ክፍል ነው። ይህንን ተቆጣጠረው ማለት መቶ በመቶ ይዞታል ማለት ነው።

ዛሬ አብዛኛው በዚህ ውስጥ ነው ያለው። ስለዚህ እዚህ ልብ እና ሆድ ውስጥ በሚመታበት ግዜ መብላት፣ ማቃጠል፣ መውረር የተለየ ባህሪያቱ ነው። መገለጫው ነው። በዚህ ግዜ አድፍጧል፣ ተቀምጧል፣ መኖርያ አድርጎታል ማለት ነው። ለየው ማለት ነው በቃ። ከዛ በኋላ ማዳከም የሚለው ቃል ተከታይ ይሆናል። በጸሎት ቦታ ላይ ማዳከም፣ እየገረፈው ማዳከም፣ ትዕዛዝ እየሰጠው ማዳከም፣ ጸጥ በል አትረብሸኝ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም አዝዣሀለው፣ በድንግል ማርያም ሥም አዝዣሀለው ብሎ በመቁጠርያ ሲመታው የመፍራት ባህሪ እየተሰማው ይመጣል። ጫን ያለ ምት ስንመታው እዚህ ሆድ አከባቢና ግራና ቀኝ ትከሻ፣ በማጅራት አከባቢ፣ ራስ ላይ እንደዚህ ስትቀውረው ቶሎ ብሎ ነው የሚለቀው። ወደ ግንባር ላይ ውጣ ስንለው ልክ እንደሚንቀሳቀስ ነፍሳት ሆኖ ወደ ግንባር ላይ ሲወጣም ሊሰማን ይችላል። ከዛ በኋላ እዛ ላይ ታስረዋለህ። ግንባር ላይ መታሰሩ ደግሞ ዋናው ጥቅሙ ምንድነው? አንተ የምታየውን አያይም ስለምትሰግድ፣ ስለምትጸልይ አንተ የምትመለከተዉን አይመለከትም። ከዓይን ውጣ ትለዋለህ፣ ከጀሮ ውጣ ትለዋለህ። ግንባር ላይ ይታሰራል። አሁን ስትሰግድ አብሮ ይሰግዳል። አልሰግድም ብሎ የወደቀ መንፈስ ስለሆነ በዚህ ጊዜ ይቃጠላል። ከዛ በኋላ እንዲህ እየቀጠቀጥከው በመቁጠርያ ስታሰለቸው ከጥቂት ግዜ በኋላ ስለሚደክመው በልብህ ውስጥ፣ በሕሊናህ ወይም በጀሮህ ውስጥ መናገር ይጀምራል። ከየት ነህ የመጣሀው? የዘር ነህ?፣ የቤተሰብ ነህ ? ከየት ነህ የመጣኸው? ስትለው ለራስህ ይነገርሃል ሌላ ጠያቂ አያስፈልግ።

11.3 መቁጠሪያን ለመጠቀም

✔ ከገዛችሁት በኋላ በቤተክርስቲያን አባቶች አስባርኩት።

✔ ቤት ይዛችሁትም ስትመጡ ከጸሎት ቦታ ውጪ አታስቀምጡት

✔ በመቀጠል 41 ወይም 64 የአምልኮ ስገዱበት

✔ የዕለቱን ጸሎትና ምስጋና ካደረሳችሁ በኋላ በስመ መለኮቱ ባርኩት

- ቅዱስ አዶናይ
- ቅዱስ ጸባኦት
- ቅዱስ ኤልሻዳይ
- ቅዱስ ያሕዌ
- ቅዱስ ኢየሱስ
- ቅዱስ ክርስቶስ
- ቅዱስ አማኑኤል
- ቅዱስ ኢያኤል
- ቅዱስ ታዳኤል
- በአብ ፤ በወልድ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም

- በቅድስት ሥላሴ ስም
- በጌታችን መድሃኒታችን በኢየሱስ መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ስም
- በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስምና የቅዱሳን ስም ወዘተ..

የተባረከ ፣ የተቀደሰ ፣ እግዚአብሔርም የወደደው ፣ ኃይለ መለኮቱም ያረፈበት ፣ የጸጋውና ሞገሱ ክብር የተገለጠበት ፣ የዲያቢሎስንም ክንድ የሚሰበር ይሁን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክብር

አሜን ትሉና ትባርኩታላችሁ።

✔ በመቀጠል ጸሎት ቤት የሚቀመጥን ቢሆን ቅባዕ ዘይትን ካልተገኘ እምነት ትቀቡታላችሁ።

11.4 ምን ምን እያልን እንቀጥቅጥ?

❖ ይህንን ለመመለስ ሕይወታችንን ማየት ነው። ከውስጥ ያደፈጠ ጠላት በሕይወታችን ምን ምኑ ላይ አጥቅቶናል? የሕይወታችን አኗኗር የቱ የቱ ላይ ተሰነካከለ? ምን ችግር ደረሰብን? የሚሉትን መሰል ጥያቄዎች አሰናስለን የመሸገውን ክፉ መንፈስ በስመ ኃይሉ መቀጥቀጥ ነው። ለምሳሌ

✓ ያደፈጥክ የቤተሰብ ዛር ፣ መተት ፣ ዓይነጥላ ፣ ቡዳ ፣ ክፉ መንፈስ ፣ ጤናዬን የምትነካ ፣ ሰላሜን የምታበላሽ ፣ ችግር የሆንክብኝ ፣ ጭንቀት የሆንክብኝ ፣ ደስታዬን የነጠክ ፣ ቤተሰቤን የበተንክ ፣ ዕድሌን የዘጋክ ፣ ትምህርቴን ያበላሸህ ፣ ስራዬን ያከሸፍክ ፣ ምቀኛ የሆንክብኝ ፣ ጠላቴ የሆንክብኝ ፣ በሰውነቴ ውስጥ ያደፈጥክ ፣ በቤቴ ውስጥ የመሸክ ፣ በቤተሰቤ ውስጥ የተደበክ ...ወዘተረፈ

የሥላሴ ስም ያንድድህ ፣

የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያሳድህ ፣

የእመቤታችን ወላዲተ አምላክ ስም ያቃጥልህ ፣

እንዳሰርከኝ የሊቀ መልዐኩ ቅዱስ ሚካኤል ስም ይሰርህ ፣

እንዳሰቃየከኝ የብስራተ መልዐኩ ቅዱስ ገብርኤል ስም ስልጣንህን ያፍርሰው

በጸባኦት ፣ በአዶናይ ፣ በኤልሻዳይ ፣ በያህዌ ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ፣ በአማኑኤል ስመ መለኮት ያደፈጥክ ሰይጣን ተቃጠል

በወላዲተ አምላክ ፣ በቤዛዊት ዓለም ፣ በቅድስት ኪዳነ ምሕረት ፣ በእናታችን ድንግል ማርያም ሰመ ጸጋ የተደበክ አጋንንት ስራህን ታቆማለህ

ሐሳቤ ውስጥ ሐሳብ የሆንክ ፣ አካላቴ ውስጥ አካል የሆንክ ፣ ተመሳስለክ የቀመጥክ ጠላት ፣ በመድሃኒተ ዓለም በኢየሱስ አምላክ ክርስቶስ ስም ግንባር ላይ ውጣና ታሰር ፣ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ታስረሃል። በወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ስም ታስረሃል።

እንዲህ እያላችሁ ስትቀጠቅጡት

❶• ጀርባን መውረር ማሳከክ

❷• እንደ ድንጋይ መክበድና ስሜት አልባ መሆን

❸• ልክ እንደ እሳት ማቃጠልና መብላት

❹• አስቀድሞ ያልነበረ ሽፍታ ፣ ብጉር ፣ እብጠት ፣ ቁስል መውጣት

❺• ቦታው ላይ ልክ ጸጉር የወጣበት ይመስል መጥቆርና ጥላሸት መልበስ

እና ሌሎች ተመሳሳይ ምልክቶች ይታያሉ። እነዚህ ምልክቶች ሳትሰግዱና ሳትጸልዩ ዝም ብላችሁ ብትቀጠቅጡት አይታዩም።

ቅዱስ ቃሉ እንደዚህ ይለናል < የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ > አፌሶን 6፥10-18

ክፍል – ፲፪

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ?

12.1 የጸሎት ቤት መርሃ ግብር

የጸሎት ክፍሉን ካዘጋጀን በኃላ የጸሎት ፣ የስግደትና የመቁጠሪያ ምግባራችን ቀጣዩ ጉዳይ ይሆናል። ስለዚህ እንዴት መንፈሳዊ ምግባርን በቅደም ተከተል እናድርግ ?

12.2 የጸሎት ቤት ቅደም ተከተል

1 ኛ✔ መጀመሪያ ጸሎት ቤታችሁ (ትንሽዬ ቤተ መቅደሳችሁ) ከመግባታችሁ በፊት ፊታችሁንና እጅ እግራችሁን ታጥባችሁና ንጹህ ሆናችሁ ተዘጋጁ። ሕልመ ለሊት (ለወንዶች) ደመ ጽጌ (ለሴቶች) በሚሆንበት ወቅት ሙሉ ሰውነት ታጥባችሁ ቢሆን ነው መልካም።

ምክንያቱም ፡ እግዚአብሔር ንጹህ መስዋትን ይወዳልና። ቤተመቅደስ እንደ ክርስቶስ ሰርግ ቤት ክብርት ነችና።

2 ኛ✔ ነጭ አልባስ ብትለብሱ መልካም። አሊያም ለቤተክርስቲያን ያዘጋጃችሁትን አልባስ። ቢጠፋ ቢጠፋ ግን ነጠላ አይጠፋም።

ምክንያቱም ፡ ክርስቶስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ብሏልና ነጭ ብርሃንነቱን ወክለን በእኔ የሚመላለስ ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ያለውን የተስፋውንና የቃልኪዳኑን ቃል እንይዛለንና፤ ብርሃንነቱን በነጭ አልባስ እንገልጻለን።

3 ኛ✔ እንደ ገባን በመቆሞ ልክ ከሥላሴ ምስል ትይዩ እንሆንና ሶስት ጊዜ እናማትባለን። ካማተብንም በኋላ በቅዱሳን ስሞቹ ጸሎታችንና ስግደታችንን እንባርካለን። ለምሳሌ፦ እንደዚህ ተብሎ ይባረክማል!

ቅዱስ እግዚአብሔር

ቅዱስ ኃያል

ቅዱስ ሕያው

ቅዱስ ጸባኦት

ቅዱስ አዶናይ

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ ያሕዌ

ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል

ቅዱስ ኢያኤል

ቅዱስ ማስያስ

ቅዱስ ታዳኤል (ሌላም መለኮተ ስሞቹን መጨመር)

በአብ ፣ በወልድ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም

በአጋእዝተ ዓለም ቅድስት ሥላሴ ስም

በእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም (ሌሎች ቅዱሳንን መጨመር)

'የተባረከና የተወደደ ፣ ኃየለ ቅዱስ መንፈስ ያረፈበት ፣ የፍቅሩም ስጦታ ያልተለየው ፣ የመለኮቱም ሥልጣን የተገለጸበትም ፣ እግዚአብሔርም በፊቱም የተመለከተውና እንደ አቤል መስዋት የተቀበለው ፣ የክፉ መናፍስታንን ርኩስ ክንድና ጉልበት የሚሰብር ፣ የአምላካችን የጽድቅ መንፈስና የቃሉንም ክብር የገለጠ ቅዱስ ስግደትና ጸሎት በልዑል ስሙ ይሁን አሜን! (ይኼን ጸሎት በሌላ በለመዳችሁትም መልክ ማድረግ መባረክ፤ አሊያም ከቅዱሳን የጸሎት መጽሐፍት ላይ መውሰድ አማራጭ ነው)'

4 ኛ✔ በመቀጠል መዝሙር 22'ን መጸለይ የግድ በቃል መያዝ አለበት። በጣም አጭር ጸሎት ነው።

[እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል። በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው። ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።]

5 ኛ✔ አስከትለን በዛው አባታችን ሆይ እንላለን

6 ኛ✔ ቀጥለን ከቆምንበት የሥላሴ ትይዩ ምስል ሆነን የአምልኮት ስግደት መስገድ።

7 ኛ✔ ስንጨርስ ተንበርክከን የሰዓቱን ጸሎት ማለትም ለምሳሌ ምሽት 3:00 ከሆነ ቅዱስ አርጋኖን ፤ ሌሊት 11:00 ከሆነ ውዳሴ ማርያም ማድረስ

8 ኛ✔ በአባታችን ሆይ የሰዓቱን ጸሎት መዝጋት

9 ኛ✔ የግል ጸሎታችንን ማድረስ (ርዕስ ሰጥተን የምናደርሰው ጸሎት)

10 ኛ✔ ካደረስንም በኋላ መቁጠሪያችንን አንስተን ከላይ በተገለጸው መለኮተ ስሞቹ በመባረክ ፤ ቅባዕ ዘይትን መቀባት። በመቀጠል አሁንም ከላይ የተገለጹትን መለኮተ ስሞችና የቅዱሳንን ስሞች በመጠቀም የመሸጉ ክፉ መናፍስቱንም እየጠሩ ተቃጠል እያሉ ጀርባን ፣ ሁለቱንም ትከሻዎች ፣ ጭንቅላትንና ሆድን መቀጥቀጥ። በተለይ ግን ጀርባን።

እንዲህ አድርግ በመቁጠሪያ ውስጣችንን ስንፈትሽ ምልክቶችን የምናገኝ ከሆነ የተደበቀውን ጠላት እንነቃበታለን። መንፈስ በመቁጠሪያ ፍተሻ ምልክት ካልሰጠ 3 ምክንያት አለው።

❶• በሚስጢር የተላከ መተት ፣ ቁራኛ ፣ ቡዳና የዛር መንፈስ ከሆነ (ምልክት ላለመስጠት ይታገላል በሚስጢር የገባ ከሆነ)

❷•ለጊዜው ዘወር ያለ መንፈስ ይሆናል (ወጣ ገባ የሚል መንፈስ)

❸• አምነንና ልባችንን ሰጥተን በተገባ የአምልኮ ልምምዱን እያደረግንም ካልሆነ ጠላት ምንም ለመኖሩ ፍንጭ አይሰጥም። ስለማያቃጥለው።

11 ኛ✔ ስንቀጠቅጥ ምልክት ከሰጠን ቅጥቀጣችንን ለጊዜው እንተውና በቅባዕ ዘይት ግንባራችንን አመሳቅለን 3'ቴ እንቀባለን። ከዛ የቅዱስ ሚካኤል ስዕለ አድንኖ ሰይፉ ላይ አንድ እጃችንን አስቀምጠን በሌላው እጃችን ግንባራችንን ይዘን ይኼ የመሸገብን ጠላት ወደ ግንባር እንዲታሰርልን ቅዱስ ሚካኤልን እንጠይቃለን። (በመለኮተ ስሞቹም በሌሎቹም ቅዱሳን ማሰር ይቻላል። የእምነት ጉዳይ ነው።)

አንድ ነገር እናስተውል፡ ቃሉ የሚለው ስጡ ይሰጣችኀል ነው። እኛ የእግዚአብሔርን ስንሰጥ እግዚአብሔር ደሞ የኛን ይሰጠናል። አሁን ታሰር ብላችሁ በእምነት ከጠየቃችሁ የተቀረው የሰማይ ጉዳይ ነው። የእናንተ ድርሻ ግማሹን መሙላት ነው። የተቀረው እኛን ለማዳን የሚችኩሉት የሰማይ ኃይላት ጉዳይ ነው። ስለዚህ የሰማይ ጊዜውን ለሰማይ ተዉት።

ሌላው እራሱ መንፈሱም ታሰሬያለሁ ሊላችሁ ይችላል። ማድመጡ አያስፈልግም። በቃ እርሱን ወደ ጎን ትታችሁ ዝም ብላችሁ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ብቻ ስጡ።

12 ኛ✔ በመቀጠል በዛው የቅዱስ ሚካኤል ስዕለ አድንኖ ላይ ግንባራችሁን እያስነካችሁ የአምልኮ ስግደት ስገዱ። ግንባር ላይ ስላሰርነው፤ ግንባራችንን ምስሉ ላይ እያስነካን ስንሰግድ በጣም ይቃጠላል። አስቀድሞ ከሰገድነው የአምልኮ ስግደት የሚለየው ይኼ መንፈሱን ካዳከምን በኋላ አብረኸኝ ስገድ ብለን ትዕዛዝ ሰጥተን ስለምንሰግድ ነው። ከዚህ በኃላ በመቁጠሪያ ስትነርቱት ስለታሰረ በጣም ኃይልና አቅሙን እያደከማችሁበት ትመጣላችሁ።

13 ኛ✔ ጸሎታችንንና ስግደታችንንም ተቀበለን ብለን እንጸልይና በአባታችን ሆይ እንዘጋለን።

- ተጨማሪ በዛው የንስሐና የሌሎችንም ጸሎታት የምናቀርብ ከሆነ ጸሎቱን ሳንዘጋ እንቀጥላለን።

ለምሳሌ፦ ቀኑ 19 ከሆነ ከአምልኮ አስከትለን 6ኛው ቅደም ተከተል ላይ ተመልሰን ለቅዱስ ገብርኤል የክብር እንሰግዳለን። ከዛ 9ኛው ቅደም ተከተል ላይ ስንደርስ የግል ጸሎታችንንም እናቀርብለታለን።

- ይህ የዘወትር የአምልኮ የቤት ውስጥ ቅዱስ መንፈሳዊ ልምምድ ነው። ሌሎቹም የንስሐና የቅዱሳን ይህንን ከማድረጋችሁ አስቀድሞ ንስሐ ተቀብላችሁ ቢሆን መንፈሱ ሙሉ በሙሉ በእናንተ ላይ አቅም ያጣል። በኋላም በዚህ ሰማያዊ ልምምድ ጸንታችሁ እየቆያችሁ ሱባዔ እየያዛችሁ ስለ ወደፊቱ ደግሞ መረጃ ጠይቁ። በምታገኙትም ምሪት እየሄዳችሁና ሥጋና ደሙን በተደጋጋሚ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በመውሰድ ሙሉ በሙሉ ዲያቢሎሱን እንጥለዋለን። ለመንግሥቱም የበቃን ልጆች እንሆናለን። ምክንያቱም

"በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥37)

12.3 የመለኮተ ስሞች ትርጓሜ

ቅዱስ ጸባኦት ፦ የሠራዊት አለቃ እግዚአብሔር

ቅዱስ አዶናይ ፦ ከሁሉ በላይ ያለ እግዚአብሔር

ቅዱስ ኤልሻዳይ ፦ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር

ቅዱስ ያሕዌ ፦ ያለ የነበረና የሚኖር ሕያው እግዚአብሔር

ቅዱስ ኢየሱስ ፦ መድኃኒት የሆነ

ቅዱስ ክርስቶስ ፦ በሥጋ የተገለጠ የተቀባ ንጉሥ

ቅዱስ አማኑኤል ፦ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ሆነ

12.4 ምግብ ስንበላ ምን ብለን እንባርክ?

በአብ

በወልድ

በመንፈስ ቅዱስ ስም (ሦስቴ)

በአጋእዝተ ዓለም ሥላሴ ስም

ቅዱስ አዶናይ

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ ያሕዌ

ቅዱስ ጸባኦት

ቅዱስ አማኑኤል

ቅዱስ ኢያኤል

ቅዱስ ማስያስ

ቅዱስ ታዳኤል

በቅዱስ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም

በቅድስት እናትህ በእመቤታችን ድንግል ማርያም ስም

(የሌሎችንም ቅዱሳኑ ስም መጨመር)

(መዝሙረ ዳዊት ምዕ. 23)

1፤ እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።

2፤ በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።

3፤ ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።

4፤ በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።

5፤ በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።

6፤ ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

<< ማዕደ አብርሃምን የባረካችሁ አጋእዝተ ዓለም ሥላሴ ሆይ የኔንም ማዕድ እንዲሁ ባርኩልኝ ጌታዬና አምላኬ ንጉሴም ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፥ በምድርም ሳለህ ለተከተሉህ ሁሉ በሰማያዊ ቃልህ ዓሳዎቹንና ቂጣዎቹን ባርከህና ቀድሰህ በብዙ እንዳጠገብካቸው፥ እኔንም እንዲሁ አድርግልኝ ለሥጋዬ የሆነውን ምግብ የሰጠኸኝ ጸባኦት አባት ሆይ፥ ለነፍሴ ከሚሆነው ቅዱስ ቁርባንህ እንዳልርቅ በመንፈስ ቅዱስ አጥር በፍቅርህ

ክበበኝ ወደ ተራቡትም እሄድ ዘንድ፤ የተጠሙትንም እመለከት ዘንድ፤ ውስጤን አንተ በመለኮትህ ምሪት፣ በቸርነትህ ኃይልና በርህራሄም ጸጋ ሞልተህ ያዘው። አሜን! >>



ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ?

13.1 አጋንንትን ስለማሰር

"እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።" (የሉቃስ ወንጌል 10፥19)

ይኽንን ቃል ሰው አይደለም የተናገረው። ዓይኖቹ የፍቅር ጨረር የሚለቁ፣ እጆቹ በቸርነት ኃይል የሚዳብሱ፣ እግሮቹ ወደ ተጨነቁት የሚሄዱ፣ ልቡ በገርነትና በምሕረት የተሞላው፣ የመድኃኒዓለም ቃል ነው። የሚጎዳችሁ የለም እኮ ነው እናንተ። ስታመልኩ፣ ስትሰግዱ፣ ስትጸልዩ ፍቅሩን አስቀድሙ። ታዲያ ያኔ ምን ያሰጋናል? ቆይ እስኪ ልጠይቃችሁ። ሰይጣን ስትሰግዱና ስትጸልዩ ምልክት ካሳየ እንግዲያስ እረኛችን እግዚአብሔር የሚያደርገውን እንደምን ያለውን ነው? ይኽንን ብቻውን ማሰብ በራሱ የውስጥ ኃይልን ይሰጣችኀል።

"በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።" (መዝሙረ ዳዊት 23፥4)

ይኸውላችሁ

ሰጠነችሁ ያለው እርግማን አይደለም። ችግር አይደለም። መውደቅን አይደለም። የሰጠን ሥልጣን ነው። ሊያውም በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ የሚነግስ።

ኃይል የምንለው መንፈሳዊ ጉልበትን ለመረከብ ጊዜ ያስፈልጋል። ስትሰግዱና ስትጸልዩ እኮ ዲያቢሎሱ የሚረበሸውና የሚበጠብጠው ተመቻችቶ እንዳይቀመጥ እረፍት ስለምትነሱት ነው። በአምልኮ ውስጥ ዲያቢሎስ ሲረብሻችሁ በእውኑ ደስ ይበላችሁ። ምክንያቱም ከውስጣችሁ ቤት ልታስወጡት እየታገላችሁት ነውና።

ክርስቶስ የሰጠንን የሥልጣን ኃይል ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያድግ እንጂ ታሸጎ እንደተቀመጠ ንብረት በአንዴ የምንቀበለው አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከጊዜ ወደ ጊዜ በበረከትና በጸጋው መገለጥ እያለፈ ከውስጣችን የሚያድግ ጉዳይ ነው።

አጋንንትን ለማሰር የቃለ-ኪዳን ጸሎት እናቀርባለን።

ቃለ-ኪዳን ማለት ከእግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር ቅዱሳን ጋር ቃል የመገባባት ጸሎት ማለት ነው። የፍቅር ጸሎት ነው። የእምነት ጸሎት ነው።

13.2 አጋንንትን ለማሰር

- የዕለቱን ስግደትና ጸሎት ካደረስን በኋላ ቅባዕ ቅዱስ አንስተን ግንባራችንን 3 ጊዜ በአምሳለ መስቀል አድርገን በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንቀባለን
- አንድ እጃችንን የቅዱስ ሚካኤል ምስል ላይ ሌላውን የቀባነው ግንባራችን ላይ እናደርጋለን
- ሊቀ መልአኩን በቃለ ኪዳን ጸሎት እንማጸናለን

< የእግዚአብሔርን ሕዝብ የምትጠብቅ ኦ ታላቁ መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ፤ በሰማይ ታላቅ ሰልፍ በሆነ ጊዜ ከፊት ቀድመህ ዘንዶውንና የጽልመት አለቆቹን እንዳሸነፍክ፤ እንዲሁ በኔም ሕይወት ከፊት ቅደምና በዘመኔ የሚጣሉኝን ርኩሳን በእሳት ዛንጅር እሰርልኝ። ሚካ-ኤል በተሰኘው የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያሳስበውን ስምህን ስጠራ ኃይለ መንፈስ ቅዱስን ላክልኝ። ቅዱስ ሚካኤል ሆይ፤ የቸርነት መልአኩ ሆይ፤ በጸሎቴ ጊዜ የሚረብሸኝን፣ የሚያስታጉለኝንም የሚበረታታብኝን ክፉ መንፈስ አንተ በሰይፍህ ጣልልኝ። የእግዚአብሔር ሕዝብ የምትመራ አንተ አለቃ ሆይ፤ እኔንም ከከበቡኝ የጨለማ ጠላቶቼ መካከል በብርሃን ምራኝ። በውስጤ የመሸገን መንፈስ ያየሁትን እንዳያይ ዓይኑን አጨልምበት። የሰማሁትን እንዳይሰማ ጆሮውን ዝጋበት። የማስበውን እንዳያውቅ ወደ ግንባሬ አምጥትህ በመንፈስ ሰንሰለት እሰረው። የእግዚአብሔር አገልጋይ ብርቱው አባቴ ሚካኤል ሆይ በነገድህም ፊት ቆመህ በጸለይህም ጊዜ እኔን ደካማውን አስብ። ሚካኤል ሆይ፤ እንዳትረሳኝ ብዬ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተማጸንኩህ። ሚካኤል ሆይ፤ ኃይልህንም ኃይሌ አድርገህ ጠላቴን ታርቀው ዘንድ በወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ስም እለምንሃለሁ። ሚካኤል ሆይ፤ ከኃጢአቴም ብዛት እንዳትተወኝ ፣ በክፋቴም እንዳትረሳኝ ስለ ስምህ ኪዳንህን አስር ዘንድ በወዳጅህ አጽናኙ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ስም እማለድሃለሁ። ሚካኤል ሆይ፤ በስዕልህ ፊት ተንበርክኬ የምነግርህን ታስብ ዘንድ በእግዚአብሔር ክብር ለነገሱ ቅዱሳን ስም እለምንሃለሁ። ሚካኤል ሆይ፤ ርኩሱ በኔ ላይ እንዳይሰለጥን ሰይፍህን ትጥልበት ዘንድ በቅዱሳን ሐዋሪያት ስም እማልድሃለሁ። ሚካኤል የኔ አባት ተከተለኝ አደራህን "

(ለሌሎች ቅዱሳንም በተመሳሳይ በቃለ ኪዳን ጸሎት በማሳሰብ መንገር እንችላለን)

- አስከትለን የቅዱስ ሚካኤልን ምስል ምንጣፋችን ላይ አኑረን ግንባራችንን ልክ ሰይፉ ላይ እያስነካን 'ውስጤ የተደበቅ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አብረኸኝ ስገድ' ብለን የአምልኮት እንሰግዳለን።
- በመቀጠል ታስሮ እንዲሰግድ የተገደደውን መንፈስ በመለኮተ ስሞችና በቅዱሳን ስም አዘን፤ በመቁጠሪያ እንቀጠቅጣለን።



ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታንን ለማስቆም ምን እናደርግ?

14.3 ቅዱስ ቁርባን

ከ ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ሲሆን፤ ቁርባን የሚለው ቃል የሱርስት ቃል ሲሆን በቁሙ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መንፈሳዊ አምኃ፣ መስዋት፣ መባዕ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ይቀርብ የነበረው የመስዋዕት ቁርባን፤ ከበግ፣ ከላምና ከተለያዩ የእንስሳት ነበር። በሐዲስ ኪዳን ግን እንስሳት በቤተ መቅደስ ውስጥ ቁርባን(መስዋዕት) ሆነው አይቀርብም፤ መስዋዕት ሁሉ በክርስቶስ ሥጋና ደም ተጠቅሏልና።

ቅዱስ ቁርባን ሕይወት ነው። ቅዱስ ቁርባን የዘላለማዊነት ማህተም ነው። ቅዱስ ቁርባን የክርስቲያን ኃይል ነው። የጸጋው ምንጭ ነው። የቃልኪዳን ስጦታው ነው። ምርኩዝ ዋሱ ነው። ያለ ቅዱስ ቁርባን ክርስትና ፉርሽ ነው። ክርስትና ክርስቶስነት ነውና። ክርስቶስነት እንኪያስ ሥጋና ደሙን በመቀበል ውስጥ ክርስቶስን መልበስ ነው።

(የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6)

54፤ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።

56፤ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።

14.4 የቅዱስ ቁርባን 7 ጥቅሞች

14.2.1 **አንደኛ ኃጢያትን ለማስተሰረይ፡–** ሓጥያት ተሰረየ ማለት ካንተና ከልጆችህ፤ ከቤትና ከኑሮህ፤ ከታሪክህና ከዘመንህ ሁሉ ተወገደ ማለት ነው። ኃጢያት ተሰረየ ማለት በሚቀጥለው ዘመን ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳትና እንቅፋት ቆመ ማለት ነው። የዲያብሎስ ሸምቅ ውግያና ስልቱ ሁሉ በሕይወትህ ያዘጋጀው መዝገብ ፈረሰ ማለት ነው።

14.2.2 **ሁለተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ለሕይወታችን አስፈላጊነት፡–** ሁለተኛ እና በጣም ትልቁ በሕይወታችን ውስጥ ፍቅር እንዲኖር የክርስቶስ ሥጋና ደም ያስፈልገናል። ፍቅር እንዲኖር። እግዚአብሔር ፍቅር ነው የሚል ቃል በዮሐንስ መልዕክት ላይ ታገኛለችሁ። እግዚአብሔር ምንድ ነው? ፍቅር ነው። ታድያ ከእርሱ ጋር እርቅ ሳናደርግ፤ በሰውነታችን ውስጥ ስፍራ ሳይይዝ፤ በባህሪያችን ውስጥ ሳይገባ፤ በሚስጥረ መለኮት የሰጠው ሥጋና ደሙን ሳንቀበል አሁን ከዚህ ትውልድ ፍቅር ይጠበቃል ወይ? እንዴት ይሆናል? እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ፍቅር ሲጠፋ የክርስቶስ ሥጋና ደም ያስፈልገናል። እንዲህ ብለን ወደሱ እንጠጋለን "አቤቱ ጌታ ሆይ ፍቅር ከህይወቴ ጠፍቷል።" እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ንቁ የሚለው በዚህም ጭምር ላይ ነው። ከቤተሰብህ ፍቅር ሲጠፋ <ጌታ ሆይ ፍቅር ሁነኝ> ማለት አለብህ። በውስጤ ውስጥ እደር ባህርያቴን ለውጠው፤ ሰማያዊ የሆነ ስጦታህን አካፍለኝ፤ የቸርነትህ ጸጋ ከኔ ጋር ይሁን፤ ሁሉ ግዜ በሃሳብህ ባርከኝ፤ ፍቅርህ ከሁሉ በላይ የሕይወቴ ፈር ይሁን ብለህ ቅዱስ ቁርባን ስትወስድ ፍቅሩን ይመልስልሃል። በፍቅርህ ውስጥ ጠላት የሆነውን ኃይል ከሕይወትህ ያስወግደዋል። በዚህ ግዜ እንግዲህ ለሀገርህም፤ ለወገንህም፤ ለህዝብህም፤ ለጎረቤትህም፤ ለጠባይህም፤ ለቤትህም፤ ለገንዘብህም ፍቅር ትሆናለህ ማለት ነው። ገንዘብ አንተ አፍቅረኸው ሳይሆን ገንዘብ አንተን አፍቅሮ ወደ አንተ ይመጣል። ኑሮ አንተ አፍቅረኸው ሳይሆን ኑሮ አንተን አፍቅሮ ወደ አንተ ይመጣል። እንጀራ አንተ ወደኸው ሳይሆን እንጀራው አንተን ወዶ ወደ አንተ ይመጣል። ግዜ አንተ ወደኸው፤ አንተ አቅደኸው ሳይሆን ግዜው አንተን ለመርዳት ወደ አንተ ይመጣል። በእያንዳንዱ ግንኝነቶችም ውስጥ ሰማያዊ ፍቅር እስካለህ ድረስ ተፈጥሮዎች ያገለግሉሃል። እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን። እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

14.2.3 **ሦስተኛ ቅዱስ ቁርባን የሚያስፈልገን ሰውነታችን ሲከብደን ነው፡–** ሰውነት ሲከብድ፤ መጫን ሲጀምር፤ ውስጣዊ ህይወትህ መረጋጋት ሲያቅተው በዚህ ጊዜ ማቴዎስ ወንጌል ላይ የተናገረው ቃል ትዝ ሊለን ይገባል። የማቴዎስ ወንጌል

ምዕራፍ 11 መጨረሻው ላይ እንዲህ ይላል ‹‹እናንተ ሸክም የከበዳችሁ ወደኔ ኑ››። ምን የከበዳችሁ? ፡ ሸክም። የግዜ ሸክም፣ የኑሮ ሸክም፣ የትውልድ ሸክም፣ የዓመታትን ሸክም። ስንት ዓመታቶች አልፈው፤ ዛሬ

እየከበደን እየከበደን የመጣውን ሸክማችንን ማን ይቻለው? እኛ ነን የምችለው? ምድሪቱ ነች የምትችለው? ኑሯችን ነው የሚችለው? ገንዘባችን ነው የሚችለው? ማን ነው የሚችለው?

በእርግጥ ተናገሩ ብንባል የፈጠረን አምላክ ይችልልናል ነው የምንለው። በእውነታና በሕይወት ውስጥ ባለው ትርጉም ውስጥ ግን የሚታይ ምላሽ የለንም። ስለዚህ በሸለቆ ውስጥ ሆነን ሰማያዊ ነገር አልታይ አለን። ሲከብደን ቅዱስ ቁርባን ያስፈልገናል። ምን ማለት ነው እንግዲህ? ሸክም ማራቅያ ነው ማለት ነው።

14.2.4 አራተኛ በረከት ከሕይወታችን ሲጠፋ፡– በረከት ከሕይወታችን ሲጠፋ የበረከት አምላክ ሕይወታችንና ኑሯችን ውስጥ እንዲኖር ቅዱስ ቁርባን ያስፈልገናል። በረከት ከምናችን ሲጠፋ? ከህይወታችን፣ ከኑሯችንና ከቤተሰባችን ሲጠፋ። ያኔ አንድ ነገር ገብተዋል ማለት ነው። የበረከት ጠላት በዙሪያችን አለ ማለት ነው። እንኪያሳ በበረከት ጎዳና ውስጥ እንጀራን ለብዙ ሺ ህዝብ የመገበ አምላክ ለኛም ሊሰጠን እንደሚችል ልቦናችን ማሳመን መቻል አለብን። ስለዚህ "ጌታ ሆይ አንተ በረከት ንጉሥ ነህ የጎደለውን በረከቴ አንተ ሙላልኝ፤ የበረከት ጠላትን ኃይል አርቅልኝ" ብለን እሱ ተማፅነን ቅዱስ ቁርባን ስንወስድ በረከታችን ይመለሳል።

14.2.5 አምስተኛ መልካምና ጥሩ ዘር ለማግኘት፡– መልካም ትውልድ ለማፍራት ቅዱስ ቁርባን ያስፈልጋል። መልካም ትውልድ፤ የእግዚአብሔር የሆነ ትውልድ፤ የሰማይ አምላክ የሆነ ትውልድ። ዛሬ በአብዛኛው ከዚህ መንፈሳዊ በረከት ርቆ የተወለደው ቃልቻ ሆነ፤ ጠንቋይ ሆነ፤ መተተኛ ሆነ። ከዛም ደግሞ አልፎ ተርፎ እንዲሁም የተወለደው የመተተኞች፤ የአስማተኞች መንፈስ መኖርያ ሆነ፤ የዛርና የውቃቤ መጫወቻ ሆነ፤ የክፉ ባህርይና የክፉ ጠባይ መጫወቻ ሆነ። ይህ ሁሉ ከቤተሰብ መንፈሳዊ ትከሻ አንፃር ያለው ጉዳት ነው። አብዛኛው ወላጅ እያወረሰ ያለው ሰማያዊ ነገርን ሳይሆን፤ ሰማያዊ ስጦታ ሳይሆን ክፉውን ነው የምናወርሰው። ይህንን ውርስ ለመከላከል ለልጆች ቅዱስ ቁርባን ሊወሰድላቸው ይገባል።

<u>በሁለት አይነት መንገድ።</u>

♦ አንደኛ ከመወለዳቸው በፊት ቤተሰቦች ቅዱስ ቁርባን ለሚወለዱት ገና ለሚፀነሱት አስበው ቅዱስ ቁርባን መውሰድ አለባቸው። ክፉ መንፈስ አብሯቸው ከማኅጸን ጀምሮ እንዳይወለድ

♦ ሁለተኛ ከተወለዱ በኋላ ለልጆቻቸው ቅዱስ ቁርባን መውሰድ የሕይወት መርሃቸው ማድረግ አለባቸው። ሕይወታቸውን ከማለዳው ክርስቶስ እንዲመራው

14.2.6 ስድስተኛ ቅዱስ ቁርባን የሚወሰደው የእግዚአብሔርን መልስ ስንፈልግ ፡- ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ስትጀምሩ በፍፁም ከሰው ልጅ ጠባይ ባህሪ ጋር አትስማሙም። ስለዚህ ብቸኝነት ይሰማቹሃል። በዚህ ግዜ "ጌታ ሆይ ዓለሙ ከኔ ሸሽተዋል አንተ ከእኔ ጋር ሁን" ማለት እንጀምራለን። ልክ በዚህ ወቅት የሕይወት ደስታ እና እርካታ አንድ ሺህ ሰው ከከበበን ይልቅ ለብቻችን ከክርስቶስ ጋር የምንኖረው ኑሮ ያረካል። ያ አንድ ሺህ ሰው ቢከብህ እየተቸ፤ በጎሪጥ አፉን እያጣመመ፤ ዓይኑን እያጨነቆረ ነው የሚያይህ።እግዚአብሔር ግን በብቸኝነት ውስጥ ብርሃን ይሰጥሃል። ይሄ ነው የሱ ልዩ

ሞጎስ። መልሱንም በራእይ ወይም በህልም ስንጠብቅ ተገቢ በሆነ ጊዜና ሰዓት እግዚአብሔር ይሰጠናል። ውስጣችን መቀደስ ሲጀምር ከውጪ ያለውን እግዚአብሔር መሪ ይሆናል ማለት ነው። እያሱ ህዝቡን ሲመራ፤ በመፅሓፈ እያሱ ምዕራፍ አንድ ላይ አንድ ታላቅ ድምፅ እንሰማለን እንዲህ ሲል ‹‹በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ።›› በቃ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ የሚለውን ድምፅ የሰማው ማን ነው? እያሱ ነው። የእስራኤልን ህዝብ ወደ ምድረ ርስት ለመውሰድ በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ የርስት ባለቤቶች እንዲሆኑ ለማድረግ ባደረገው ጉዞ ውስጥ ማንም አይቋቋምህም የሚለውን ድምፅ በሕይወቱ ውስጥ እግዚአብሔር ሰጠው። እኛ የምናወርሰው ነገር አሁን ምን አለ?። በመሠረቱ እኮ የእግዚአብሔር ህዝብ መስጠት እንጂ፤ እየሰጠ የሚሄድ እንጂ እያጣ፤ እየደኸየ የሚሄድ አይደለም። እኛ ግን እያጣን፤ እየደኸየን መጣን። ውስጣችን መጀመርያ እግዚአብሔርን አጣ። ከዛ በኋላ በዓለም ላይ ባለው ነገር ላይ ምንም ባለቤትነትን አጣን። ለማንኛውም ነገር ቅጥረኞች ሆንን። ከሁሉም ደግሞ የሚገርመው እንጀራ በባህሪው ከነክፋቱ፤ ከነተንኮሉ፤ ከነምቀኝነቱ ገዛን። እግዚአብሔር የሌለበት ስፍራ እንዲህ ይሆናል። እና ሲከብደን፣ ሲጫነን፤ በአከባቢ፣ በጎረቤት፣ በሀገር ሁሉ ላይ ችግሮች ሲመጡ፤ የእግዚአብሔርን መልስ ለማግኘት ቅዱስ ቁርባን ይወሰዳል ማለት ነው። ከዛ በኋላ ችግራችንን ያስወግዳል የሰማይ አባታችን።

14.2.7 ሰባተኛ ስለዘለዓለም ሕይወት ቅዱስ ቁርባን ይወሰዳል፡– ስለምን ይወሰዳል? ስለዘለዓለም ሕይወት። የዘለዓለም ሕይወት አለህ ማለት ደግሞ ይሄ አጥፊው መንፈስ በሕይወትህ ውስጥ ስፍራ የለውም። አንተ የዘለዓለም እንጂ የግዜዎች አይደለህም። ዛሬ በየግዜው ራሳችንን እያገለባበጥን፤ ኑሯችንን ሲገለባበጥ፣ ጠባያችንን ሲገለባበጥ፣ ህሊናችንን ሲገለባበጥ፣ አመላችን ሲገለባበጥ። እንዴት ነው? እየተገለባበጥን እስከ መቸ ነው? ራሳችንን ለማግኘት ለምን አልቻልንም? ሊቆይ የሚችለው ለምን ማግኘት አልቻልንም?

የዘለዓለም ሕይወት ከውስጥህ ሲወጣ፤ የሚጠብቅህ ነገር ቢኖር እንዲሁ ትርኪ ሚርኪ የሆነ የመንደር ኑሮ ነው። የመንደር ኑሮ፤ የግዜ ኑሮ፤ የሰዓት ኑሮ። ግዜዎች ሲወድቁ አብረህ ትወድቃለህ፤ ግዜዎች ሲጠፉ አብረህ ትጠፋለህ፤ ግዜዎች ሲያርፉ አብረህ ታርፋለህ፤ ግዜዎች ሲሰደዱ አብረህ ትሰደዳለህ።

እንዴት ይሆናል ይሄ? ክርስትያኖች በሰማይ አምላክ ዘንድ ባለ በዘለዓለማዊ ሕይወት መያዝ አለባቸው። እና ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት ቅዱስ ቁርባን ይወሰዳል ማለት ነው።

"የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 16፡፥20)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር

የእግዚአብሔር ምህረት

ከሁላችን ጋር ይሁን።